በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

"ሂዱና አስተምሩ በጨለማ የነገርኳችሁን በብርሃን ተናገሩት በጆሮአችሁ በሹክሹክታ የነገርኳችሁን በሰገነት ላይ ስበኩት።"ማቴ **10÷26**

የቤተክርስትያን ታሪክ በኢትዮጵያ

የህጻናትና አዳጊ ትምህርት ክፍል

ምዕራፍ አንድ

ቤተክርስቲያን ስያሜው ትርጓሜው በተለያየ ቋንቋ በተለያየ ጊዜ ተጠቅሷል። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያልነበረችበት ጊዜ የለምና። «ቤተክርስቲያን» የግእዝ ቃል በግሪኩ ‹አቅሌስያ› ይባላል፤ ይህ ማለት ደግሞ ‹ማኅበር› ወይም ‹ጉባኤ› ማለት ሲሆን ይኸውም የክርስቲያን ስብስብ እንደሆነ ይገልጻል። (የአማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ 100 ይመልከቱ)

ቤተክርስቲያን ከአገልግሎቷ አንጻር በብሉይ ኪዳን ምኩራብ፣ ደብተራ ኦሪት፣ ቤተመቅደስ ከዚያም በሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ትባላለች። ይህ ሁሉ ስያሜ እንግዲህ ለአንድ ነገር የተሰጠ ስያሜ ነው።

‹ቤተክርስቲያን› የሚለው ቃል በስያሜው፣ በአገልግሎቷና በአሠራሯ ሦስት ዓይነት ትርጉም አለው።

ሀ. አካለ ምዕመናን ቤተክርስቲያን /ቤተመቅደስ/ ይባላል፤ 1 ቆሮ፡-6÷7፤ 1 ቆሮ፡-3÷16፤ ዮሐ.1÷19

ለ. ሕንፃው ቤተክርስቲያን /ቤተመቅደስ/ ይባላል፦ ዘፍ፡-16፤15፤ 2 ዜና፡-7፣11-16 ማቴ፡-16÷16፤ የሐዋ፡-20÷28፤ የሐዋ፡-3÷6፤ ማቴ. 26÷12

ሐ. ማኅበረ ምዕመናን /የምዕመናን ጉባረት/ ቤተክርስቲያን /ቤተመቅደስ/ ይባላል፦ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "ሁለትም ሦስትም በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ" በማለት ስለ ክርስቲያኖች ስብስብ /ማህበር ተናግሮአል። ማቴ፡-11፤20፤ 1 ቆሮ፡-16፣19፤ 1 ቆሮ፡-11፤17

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ምን ማለት ነው? እነዚህንና እያንዳንዱን ለመፍታት ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው ከሚለው እንነሣለን።

ታሪክ ማለት ከእውነተኛ መረጃ በመነሣት ስለ አንድ ሀገር፣ ሕዝብ፣ ሥራ፣ ቋንቋ ባሕል ትውፊት የምናጠናበትና ያለፈውን እና ያለውን፣ በጎውንና ክፉውን የምናይበት መንገድ ነው።

ታሪክ፦ ማለት ከጊዜ አንጻር የሚሰጥ ገለጻ ነው፤ በማለት አማኑኤል ካንት የተባሉ እንግሊዛዊ ምሁር ያስረዳሉ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ታሪክ ብዙም ከዚህ የተለየ አይደለም። በመ. ኢዮ፡-8÷8 "ዘመናችን በምድር ላይ እንደ ጥላ ነውና፤ እኛ የትናንት ብቻ ነን፤ ምንም አናውቅም" በማለት ይገልጽልናል። ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ሙሴም፦ አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችን ጠይቅ ይነግሩህማል› ዘዳ፡-32፣7 ሲል ተናግሮአል።

ታሪክ በሦስት ዓይነት መንገድ ሊገለጥ ይችላል። እሊህም፦

ሀ. በሥዕል

ለ. በጽሑፍ እና

ሐ. በቃል ናቸው።

1. የቤተክርስቲያንን ታሪክ ለምን እንማራለን?

ሀ. የሃይማኖትን /የእምነትን ታሪክ ለማወቅ

ለ. የሀገርን ታሪክ ለማወቅ

ሐ. አባቶች በየጊዜው ያስተማሩትን፣ የሕዝቡን ጠባይ ለማወቅና ማኅበራዊ ሕይወቱን ለማጥናት የሚመጣውንም ለመመርመር

መ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ያበረከተቻቸውን አስተዋጽዖዎች ለማወቅና ራሳችንን በእምነት ለማነፅ

ሠ. በመንፈሳዊ ሥራ ምሳሌዎች/አብነት ለመሆን ዕቡ፡-11÷1 - ፍጻሜ

2. የቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት ምንጮች

ሀ. የብሉይን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት /ትርጓሜ መጻሕፍት/

ለ. የቤተክርስቲያን አባቶች የጻፏቸውና የደነገጓቸው መጻሕፍት

ለምሳሌ፦ ሃይማኖተ አበው፣ ስንክሳር፣ ፍትሐ ነገሥት፣ ክብረ ነገሥት በጠቅላላው አዋልድ መጻሕፍት

ሐ. ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታና ዘመን ተገኝተው የነበሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የታሪክ ጸሐፊዎች የጻፏቸው መጻሕፍት

መ. በየጊዜው የተገኙ የክርስቲያን መቃብሮች፣ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የነገሥታት ገንዘቦች፣ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እና በቀደምት አባቶች የተሣሉ ቅዱሳት ሥዕላት

3. ታሪክን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

1. አባቶችን በመጠየቅ /ዘዳ፡-32÷/
2. ቅዱሳን አባቶች የጻፏቸውን መጻሕፍት በማንበብ
3. ታሪካዊ ቦታዎችን በማየት/ በመጎብኘት
4. በመንፈሳዊ ጉባኤዎች በመገኘትና ተከታትሎ በመማር

4. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ታሪክ የመማር ዓላማ/ አስፈላጊነት

እያንዳንዱ ሀገር የራሱ የሆነ እምነት አለው፤ የእምነቱ ታሪክ የሀገሪቱ ታሪክ እንደሆነ አውቆ ታሪኩን ይጠብቃል። ስለዚህ የመማር ዓላማችን የእምነታችን ታሪክ ማወቅ፡- ማለት ያድነኛል ብሎ ማመንም ጭምር፤ እንዲሁም ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ስንማር ስለ ቅዱሳን አባቶች አኗኗር፣ ቅድስና፣ ንጽሕና፣ ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት በማወቅ እምነታችንን የምናጸናበት፣ የዛሬና የነገ የቤተክርስቲያን ታሪክ ባለቤቶች እኛ መሆናችንን አውቀን ንሰሐ ገብተን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡረ ደሙን ተቀብለን የስሙ ቀዳሽ የመንግሥቱ ወራሽ ለመሆን ጭምር ነው።

ኢትዮጵያ ማን ናት ?

ስሙ መጀመሪያ የተገኘው ከእግዚአብሔር ነው። ይኸውም ብርሃኑን ዕለት፣ ጨለማውን ሌሊት፣ ጠፈርን ሰማይ፣ ሰውን አዳም፣ ብሎ እንደጠራው ማለት ነው። ዘፍ፡-1÷5-8፤ 5÷2 ሰው መብዛት ከጀመረ ወዲህ ግን የሰውና የቦታ ስሞች መገኘት ጀምረዋል። የሀገር ስም አወጣጡ በነገድ ስም በትንቢት ወይም በመታሰቢያነት ነው። ዘፍ፡-17÷5

የኢትዮጵያ ስያሜ መታሰቢያ ውስጥ የሚመደብ ሆኖ ቤቴል በሚለው ስያሜ አንጻር ይተረጎማል፤ ይህም ቤቴል ማለት ሀገረ እግዚአብሔር ማለት እንደሆነ ኢትዮጵያ ማለት ሀገረ እግዚአብሔር ማለት ይሆናል። ዘፍ፡-28፣19 የኢትየጵያ ስሟ የእግዚአብሔር መታሰቢያ ነው እንጂ በፍጡራን ስም የተጠራች አይደለችም። ኢትዮጵያ ተብላለች የሚለው ታሪክ ከዘመነ ካም ጀምሮ እስከ 5 ኛ ንጉሥ ሆኖ የነገሠው ኢትዮጲስ የሚባለው ንጉሥ እስከነገሠበት ዘመን ድረስ ብዙ ነገሥታቶች የነገሡባትን ብዙ ዘመናት ያሳለፈችውን ሀገር ያለ ስም አስቀርቶአታል። ነገር ግን ኢትዮጵያ በምታመልከው በእግዚአብሔር ስም የአምላክ ሀገር ተብላ ትጠራለች።

የኢትዮጵያ መጠሪያ ስሞች

1. ኢትዮጵያ የሚለው ስም ትርጓሜው፡ኢ- ማለት እግዚአብሔር
   ት- ታው /ትጉህ አብ/
   ዮ- ዮድ /የማነ እግዚአብሔር ወልድ/
   ጵ- ጵራቅሊጦስ /መንፈስ ቅዱስ/
   ያ- የእንድ አምላክ የአብ የወልድ መንፈስ ቅዱስ ሀገር ማለት ሆኖ እናገኘዋለን።
2. ኢትዮጵያ «ጱንጥ» ተብላ ትጠራ ነበር፤ ይህ ስም በቀደመ ዘመን የዚህች ሀገር ስም እንደነበር ይነገራል። ስሙም ከካም ልጆች ጋር ተመሳሳይነት አለው። ዘፍ፡-8÷6 የካም ልጆች ኩሽ ምጽራይም፣ ፉጥ፣ ከነዓይ ይባላሉ። ፉጥ የሚለው ቃል ከጱንጥ ስም ጋር ተማሳሳይነት ስላለው ነው።
3. ኢትዮጵያ «ቶኔቶር» ተብሎ ትጠራ ነበር። ይህን ስም ያወጡላት ግብፃውያን ናቸው። የቃሉም ትርጉም ሀገረ እግዚአብሔር ማለት ነው።

4. ኢትዮጵያ «የሳባ ምድር» ተብላ ትጠራ ነበር፤ ንግሥት ሳባ ሀገሪቷን ስለምታስተዳድር እና በኢትዮጵያ ምድርም የሳባ ምድር ተብሎ የሚጠራ ስፍራ ስላለም ጭምር ነው። በተጨማሪም በመዝ፡-71÷10 “የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ ነገሥታቱም ሁሉ ይሰግዱለታል” ስለሚል ነው።
5. ዐረቦች ኢትዮጵያን «አበሻ /ሐበሻ/›› ብለው ይጠሯት ነበር። አበሻ ማለት በዓረብኛ ውጥንቅጥ ቅይጥ /ቅልቅል/ ማለት ነው። የቤተክርስቲያናችን አባት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በመጽሐፋቸው ላይ ይህንን ሲያብራሩ ዐረቦች ይህን ትርጉም የሰጡት በኢትዮጵያውያን ላይ የተሳሳተ አመለካከት ስለነበራቸው ነው ብለውታል።
6. የኩሽ ሌላኛው ልጁ አቢስ ወይም ሱባታ ይባላል በአቢስ «አቢሲኒያ» ተብላለች።
7. ኢትዮጵያም «የኩሽ ምድር» ተብላ ትጠራ ነበር፤ ይህን ስም ያገኘችው መጽሐፍ ቅዱስ በሰባው ሊቃናት ከመተርጎሙ በፊት የኩሽ ምድር /ሀገር/ ተብላ ስትጠራ ስለነበር ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ /ጽርዕ/ ሲተረጉሙት የኩሽ ምድርን ኢትዮጵያ እያሉ ተርጉመውታል።
8. ኢትዮጵያ ሀገራችን «ምድረ አግዓዚያን» ተብላ ትጠራ ነበር፤ ይህንን ስም ያወጡት ከየመን የተከፈሉ ነገደ ዮቅጣኖች ያወጡላት ስም ነው። በመጨረሻም የተጠራችበት ስም ነው።
    - ኢትዮጵያ በግሪክ የታሪክ ጸሐፊዎች ኢትኦፒያ /ኢትዮጲስ/ ብለው ሲጠሯት ከሁለት የግሪክ ቃላት የወጣ እንደሆነ ይናገራሉ።

ኢቶስ እና ኦጲሲስ፡- በማለት ኤቶስ ማለት ዋዕይ በረሃማ ሞቃታማ ማለት ሲሆን

ኦጲሲስ፡- ማለት ገጸ አርዓያው /መልኩ/ የጠቆረ ሕዝብ ማለት ነው

ኦቲኦፒያ፡- ቢል የሀገሪቱ ቆላነትን ያመለክታል

ኢትኦጲስ ቢል፡- የሕዝቡን መልክ ያመለክታል፤ በፀሐይ ፊቱ የጠቆረ ሻንቅላ ማለት ነው። ይህን ስያሜ የሠጧት ለኢትዮጵያ የተሳሳተ አመለካከት ይዘው ነው። ወይም ስለሀገሪቱ የአየር ጠባይ የጠለቀ እውቀት /የታሪክ ምርምር/ ካለማድረጋቸው የተነሣ ነው።

ሀ. ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ

በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው የእግዚአብሔር ሰዎች በጻፏቸው ቅዱሳት መጻሕፍት በብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ውስጥ ስለቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ቢያንስ ከ 41 ጊዜ በላይ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህም ኢትዮጵያን ከእሥራኤል ቀጥላ ሁለተኛ ቅድስት ሀገር ያሰኛታል። የተወሰኑት ጥቅሶች እነዚህ ናቸው፡-

- 2 ዜና፡-16፤8
- 2 ዜና፡- 14፤12
- ኤር፡-38፤7 እና 10
- መዝ፡-68፤10
- መዝ፡-87፤4
- ኢዮ፡-28፤19
- 2 ነገ፡-19፤9
- አስ፡-1፤1
- አስ፡-8፤9

ለ. ኢትዮጵያ በታሪክ ጸሐፊዎች

- ከእስራኤል ወገኖች ውጭ መጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ነው። እነርሱም «ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆኖ ሰበከ» ሲል ቅዱስ አውሳብዮስ ተናግሮአል። በዚህም በመዝሙረ ዳዊት ላይ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለውን ትንቢት ፈጸመ።
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በወረደበትና 3000 ሕዝብ በተጠመቀበት ዕለት ኢትዮጵያውያንም በቦታው ነበሩ። ቅዱስ ሉቃስ ያልጠቀሳቸው ቁጥራቸው ጥቂት ስለሆነ ነው" ሲል ተናግሮአል።
- በ 391 ዓ.ም አካባቢ ግብጽን የጎበኘው ፓላዲየስ ከግብጽ ገዳማት በአንዱ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ጽፏል።
- በ 386 ዓ.ም. በቤተልሔም ከተማ የነበረው ሄሮኒመስ የተባለው ጸሐፊ ማርሴላ ለተባለች ወጣት በጻፈላት ደብዳቤ ላይ ከሕንድ፣ ከፋርስ እና ከኢትዮጵያ በየሰዓቱ ብዙ መነኮሳት ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ እንደነበረ መስክሯል።

ምዕራፍ ሁለት

ሐገ ልቡና

ሐገ ልቡና ለሰው በጥንተ ተፈጥሮው ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጠው የመጀሪያው ሕግ ነው። ይህ ሕግ ብርዕ መቅረጽ፣ ቀለም መበጥበጥ፣ ብራና መዳመጥ፣ በጠቅላላ የጽሕፈት መሣሪያ የማይሻ ነው። ሕግጋቱም በመላእክት የተጠና ስለሆነ ከተፈጥሮአቸው ጀምሮ እስከአሁን አልተለወጠም። ሰውም እንደመላእክት ሃይማኖቱን በሐገ ልቡና አውቆና ጠበቆ ፈጣሪውን ፈርቶ ሊኖር እንጂ በወረቀትና በብርዕ ሊመራ አልተፈጠረም ነበር። ሔኖክ፡-19፤22

ይህ ሕግ የነበረበት ዘመን ከአዳም አንሥቶ እስከ ሙሴ ድረስ ያለውን 4000 ዓመታት ያጠቃልላል። ይህ ዘመን በሌላ አጠራር ዘመነ አበው ይባላል። በዚህ ሕግ መሪነት ሰው ከእግዚአብሔር የተሠጠውን ሕግ ጥሶ በተፈረደበት ፍርድ እውቀት ማጣቱ እየከበደ ስለሔደ እግዚአብሔርን ለማግኘት የተቅበዘበዘባቸው የሞት መንገዶች ብዙዎች ናቸው። እነዚህም በሰማይ ሠራዊት፣ በፀሐይ፣ በጨረቃ፣ በኮከብ፣ በምድር፣ በሰው በአዕዋፋትና በእንስሳት ምሳሌ የተቀረጸና የተሠሩ ጣዖታት ናቸው።

ሐገ ልቡና በኢትዮጵያ

ሐገ ልቡና በሀገራችን በኢትዮጵያ ከኖኅ ልጆች ዘመን ጀምሮ እስከ ንግሥተ ሳባ ዘመነ መንግሥት እንደነበር ይነገራል። ከዚህ በፊት ያለው ዘመን ታሪክ በስፋት ያልተጻፈበት ጊዜ በመሆኑ ሁኔታውን ለመናገር ያስቸግራል። በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን በሀገ ልቡና የምታመልክ እንደነበረች ታሪክ ያመለክታል። አልፎ አልፎም የባዕድ እምነት እንደነበረም ተጽፏል። ይህ ማለት ኢትዮጵያ ጣኦት የሚመለክባት ሀገር አያሰኛትም።

በአጭሩ ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ በአእምሮ ጠባይዕ መምህርነት በሐገ ልቡና መሪነት በሥነ ፍጥረት ምስክርነት አምላኳን አውቃ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋ የነበረችበት ዘመን እንጂ ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት በባዕድ አምልኮ የኖረችበትና ከአምልኮተ እግዚአብሔር የራቀችበት ዘመን አይደለም። የመጀሪያዎቹ የኢትዮጵያ አቅኚዎች የኩሽ ልጆች እምነታቸው በአያታቸው በኖኅ አምላክ በአንድ እግዚአብሔር ነበር።

ነገር ግን እምነታቸው በትምህርት የተደገፈ ስላልነበረ አንዳንድ የባዕድ አምልኮ ይቀላቀል እንደነበር ከላይ ተመልክተናል። ለዚህም የሚጠቀሰው የአርዌ ንጉሥ ዘመን ነው። በዚህ በአርዌ ዘመን የሚመለከው ዘንዶ ሲሆን ይህንንም በ 1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው የንግሥት ሳባ አባት አንጋቦስ የሚሰጠውን ግብርና የሚደረገውን አምልኮት በመመልከት ከሕዝቡ ጋር በመመካከር ገድሎታል። በዚህን ጊዜ ከተገደለው ዘንዶ ደም ሲፈስ በሥፍራው ከአባቷ ጋር የነበረችው ንግሥት ሳባ ከዘንዶው በድን ብትረግጥና ደም እግሯን ቢነካት ቀንድ መሰል ነገር በእግሯ ላይ እንደተጣበቀባት ታሪኩ ይነግረናል። አንጋቦስም ዘንዶውን ከገደለ በኋላ (ከ 1020-1013) ዓመተ ኩነኔ ዓመት ያህል ነግሣ E ል። ከእርሱም በኃላ የነገሠችው ንግሥት ሳባ ነች።

ንግሥት ሳባ /1013 – 982/

- እንደ ዜና መዋዕል አጠራር ‹ሳባ›፣ እንደ ክብረ ነገሥት ‹ማክዳ›፣ እንደ ወንጌል ‹ንግሥተ አዜብ /የደቡብ ንግሥት/› ትባላለች። በኢትዮጵያ መንግሥትን ከአባቷ ከአንጋቦስ /ከተዋበያ/ ወርሳ ከኢትዮጵያ እስከ ማደጋስካር፣ የመን፣ ደቡብ ጎበጽ የገዛች ከጌታ ልደት በፊት 1 ሺህ ዓመት አካባቢ የተነሣች ንግሥት ናት። ንግሥት ሳባ ከባሪያዋ /ከአገልጋይዋ/ ከነጋድራስ ታምሪን ስለጠቢቡ ሰለሞን ጥበብ ሰምታ ጥበቡን ለማድነቅና የሚሠራው ቤተመቅደስ ለመመልከት ጉዞዋን አደረገች።
- ንግሥት ሳባ /ማክዳ/ የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት በግመሎቿ ላይ ልዩ ልዩ ገጸ በረከቶች ማለትም 797 የተለያዩ ጭነት የተጫኑ ግመሎችና ስናር አህዮች በአሽከርና በደንገጡሮቿም የከበሩ ስጦታዎችን አስይዛ 120 /ቅንጣት/ መክሊት ወርቅ አስጭና የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ከመመረቁ በፊት ኢየሩሳሌም ገብታለች።
- ንግሥት ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት በእንቆቅልሽም መፈተኗ፣ ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ እንደተረጎመላት፣ ከንጉሡም የተሰወረ ነገር አልነበረምና መልስ ያልሰጠበት የለም። ንጉሥ ሰሎሞንም በንግሥት ሳባ አስተዋይነትና ጥበብ ፈላጊነት ተደንቆ እንቁ ለጣትሽ ጌጥ ይሁንሽ ሲል እጅግ በጣም የከበረ እንቁ አበረከተላት። በተጨማሪም በኢየሩሳሌም ዴር ሱልጣንን ርስት አድርጎ ሰጣት። 1 ነገ፡-8፤20፤ 2 ዜና፡-9፤1፤ 1 ነገ፡-1 ዐ፤1-10 ከዚህ በመነሣት እንቁጣጣሽ የሚለው የመስከረም ወር መግቢያ ስም ሆኖ ቀርቶአል።
- ንግሥት ሳባ፡- ‹እኔ መጥቼ በዓይኔ አስከማይ ድረስ የነገሩኝ አላመንሁም ነበር። እነሆም እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበር። ጥበብህን ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይበልጣል። በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎች እነዚህ ባሪያዎችህ ምስጉኖች ናቸው። አንተን የወደደ በእስራኤል ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘለዓለሙ ወድዶታልና ስለዚህ ጽድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ አስነሣህ› ብላ ካመሰገነች በኋላ ያመጣቻቸውን ገጸ በረከቶች ሰጠችው። ንግሥት ሳባ ስድስት ወር ኢየሩሳሌም በቆየችበት ጊዜ ደስ ተሰኝታለች፤ ወደ ሀገሯ ትሔድ ዘንድም ዝግጅት አደረገች። ንጉሥ ሰሎሞንም በብዙ ግርማም ሸኛት፤ ለብቻዎ ፈቀቅ አድርጎም እንዳትረሺኝ አንቺ ዘርን ብታገኚ ወንድ ልጅ ከወለድሽ ወደ እኔ ይምጣ “የእግዚአብሔር ሰላም ከአንቺ ጋር ይሁን” አላት።

ንግሥት ሳባም ሰሎሞንን አንተን የማስታውስበት እግዚአብሔርን የማመሰግንበት ይሆነኝ ዘንድ ታቦተ ጽዮንን ስጠኝ አለችው። እርሱም ታቦተ ጽዮንን እንደማይሰጣት ካስታወቃት በኋላ ከዚህ በታች ያሉትን ይዛ መጥታለች።

1. ፅንስ ፀንሳ
2. የታቦተ ጽዮን የውስጥ መሸፈኛ
3. የምትወልደው ወንድ ከሆነ ለምልክት ይሆነው ዘንድ የንግሥና /የማኅተም/ ቀለበቱን ይዛ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች።

በጉዞ ላይ እያለች ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ሲሆናት በአስመራ ክፍለ ግዛት በሐማሴን አውራጃ ማይበላ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ልጇን ወለደች። የወለደችውም ወንድ ልጅ ሲሆን ስሙንም ሕብነሐኪም ብላ ጠራችው፤ ትርጉሙም የጥበበኛ ልጅ ማለት ነው። ሕብነሐኪም ከጊዜ ብዛት በኋላም ምኒልክ በሚለው መጠሪያው ሲተካ አብነ መልክ /የንጉሥ ልጅ የሚል ተጨማሪ መጠሪያ እንደነበረው ይነገራል።

ምዕራፍ ሦስት

ሕገ ኦሪት

ቀዳማዊ ምኒልክ /ዳግማዊ ዳዊት/ 982-957

ቀዳማዊ ምኒልክ ከእናቱ ጋር እስከ 22 ዓመት ሲኖር ቆይቶ አባቱን ሰሎሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ፤ ሀገሩንም ስለማያውቅ ነጋድራስ ታምሪንና ብዙ አጃቢዎችን አስከትሎም ነበር። ምኒልክም ኢየሩሳሌም እንደደረሰ አባቱ መኳንንቱንና መሳፍንቱን አስከትሎ ከፍተኛ አቀባበል አደረገለት፤ በኢየሩሳሌም ቆይታውም በሊቀ ነቢያትም ሳዶቅ አማካይነት ሕገ ኦሪትን ተማረ፤ የቤተ መንግሥት ሕጎችንና የዐበራይስጥ ቋንቋ ተማረ፤ ሰሎሞንም ቀዳማዊ ምኒልክ ልጁ መሆኑን ለእስራኤል አስታወቀ፤ እስራኤልም ተቀበሉት።

ቀዳማዊ ምኒልክ 3 ዓመት በኢየሩሳሌም ከቆየ በኋላ ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፤ ሲመለስም ከአባቱ ከሰሎሞን የተለያዩ ስጦታዎችን ተበርክተውለታል። እነዚህም፡-

- ታቦተ ጽዮንና የቤተ መቅደስ ንዋያት
- 318 ሊዎውያን ካህናትና የመጻሕፍት መምህራን
- 12 000 እስራኤላውያን /የበኩር ልጆች/
- ከሔኖክ እስከ ሰሎሞን እስከጻፋቸው ያሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
- ከሕዝቡ የተወጣጡ በኩራት የቤት እንስሳትና የተለያዩ መገበያያዎችን በመያዝ ወደ ሀገሩ ተመልሷል።

ኢትየጵያ በሰባቱ ኪዳናት

- ኪዳነ አዳምን ምልክቱ ቅዱስ ጋብቻ ማቴ፡-19፤6
- ኪዳነ ኖኅን ምልክቱ ቀስተ ደመና ዘፍ፡-9፣18
- ኪዳነ አብርሃምን ምልክቱ መገዘር /ግዝረት/ ዘፍ፡-17፤1-7
- ኪዳነ መልከጼዴቅ ምልክቱ ኅብስትና ወይን ዘፍ፡-14፤18
- ኪዳነ ሙሴ ምልክቱ ጽላት /ታቦት/ ዘዳ፡-20፤1-20 ዮሐ፡-11፤8
- ኪዳነ ዳዊት ምልክቱ የዘውድ ዙፋን ዘፍ፡-49፤9፤ ራእ፡-5፤3-5
- ኪዳነ ምሕረት ምልክቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዮሐ፡-5፤52

ኢትዮጵያ በሰባቱ ሀብታት

ኢትዮጵያ በአበው መምህርነት በሥነ ፍጥረት ምስክርነት ከአምልኮተ ጣዖት ተለይታ እግዚአብሔርን ስለተከተለችና ስላመነች እንደ አእምሮዋ ስፋት እንደ ሃይማኖቷ ጽናት የምድር አሕዛብ የሰው ልጆች ሁሉ በየወገናቸው በየቋንቋው በየሰጣቸው ምድርን ተካፍለው በየርስታቸው መኖር

ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ ከአበው የወረደውን ያልተሻረ፣ ያልተደፈረ፣ ያልተጣሰና ያልተደመሰሰ ነጻነትን፤ በነጻነትም መሠረትነት የሚገኙትን ሰባቱን ሀብታት ከእግዚአብሔር ተቀብላለች። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ሃይማኖት
2. ፍቅር
3. ስም
4. መንግሥት
5. ክህነት
6. ቋንቋ
7. ልምላሜ

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ

- የግእዝ ቋንቋ አማርኛ በቦታው እስከተተካበት እስከ 12 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የሀገሪቱ ሥርዓተ መንግሥት የሚመራበት፣ ሕብረተሰቡ በጽሑፍም ሆነ በቃል ሐሳቡን የሚገልጥበት እና የአፍ መፍቻ የምሥጢራት መክፈቻ የሠዋስው መግቻ ሆኖ የቆየ ሲሆን በሠዋስው ረገድም የአማርኛው ቋንቋ ሙሉ በሙሉ የግእዙን ሥርዓት የተከተለ ነው።
- የግእዝ ቋንቋ ትምህርት እስከአሁን በቤተክርስቲያን አማካይነት ሕያው ሆኖ ኖሯል፤ ወደፊት ይኖራል። ትምህርቱ እስከቅርብ ጊዜ ይሰጥ የነበረው በቤተክርስቲያን አካባቢው በታላላቅ አድባራትና ገዳማት ብቻ ነበር። ግእዝ ከድንጋይ ዘመን እስከ ብራና ዘመን ከብራና ዘመን እስከ ወረቀት ዘመን በሥነ-ጽሑፍ ሲያገለግል የቆየ ጥንታዊ ቋንቋ ስለሆነ ኢትዮጵያን የታሪክና የሥነጽሑፍ የሥነ ጥበብ ባለቤት አድርጓታል።
- በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በተለይም ከሰሐራ በታች ካሉት ሀገሮች የራስዋ ፊደልና ጽሑፍ ያላት ሀገር ኢትዮጵያ ናት። ጥንታዊው፣ ብሔራዊ ቋንቋዋም ግእዝ ነው። ግእዝ ማለት የቋንቋ ስም፣ የፊደል ስም፣ የንባብ ስም፣ የዜማ ስም ሲሆን ዘይቤውም አልፋ እንደ ማለት ነው፤ አንደኛ፣ መጀመሪያ፣ በኩር፣ ቀዳማይ፣ ጥንት ማለት ነው።
- አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ስለ ግዕዝ ቋንቋ ጥንታዊና ቀዳማዊ መሆኑን በግጥም መስክረዋል እንዲህ በማለት

  ከአዳም ከኖኅ ከአባት ከእናቷ

  ለሴም የታጨች ስለወበቷ

  ከንጉሡ ከእግዜር ከባለቤቷ

  ሰለተሰጠች እቴጌነቷ

  እንዲህ ብታይዋት ደሃ መስላችሁ

  ባለጸጋ ናት ግእዝ ቋንቋችሁ በማለት አስቀምጠዋል
- ግእዝ ከእግዚአብሔር ለአዳም ይሰጥም ከነገር/ከጊዜ በኋላ ይምጣም ለብዙ ጊዜ የሰው ዘሮች ለመግባቢያነት ይፍጠሩትም ትናንት በመግባቢያነትም ሆነ በጽሑፍ ቋንቋነት ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥቷል።
- የግእዝ ቋንቋን አገልግሎት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡-

  1 ብሔራዊ አገልግሎት

  2 ሃይማኖታዊ አገልግሎት ናቸው

የምዕራፍ አንድ ማጣቀሻ /ማመሳከሪያ/

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ለ 2181 ዓመት በእምልኮተ እግዚአብሔር ስትመራ ቆይታ ከእስራኤል ቀጥሎ በሊቀ ካህናት አዛርያስ እጅ በእምልኮተ እግዚአብሔር ለቆየችበት ሕገ ልቡና ክፉና በጎውን ለይቶ ለማወቅ እግዚአብሔር የሚወድደውን ለማጥናትና ለመጠበቅ አጋዥ ይሆናት ዘንድ በልዑል እግዚአብሔር እጅ የተጻፈውን የሕግ መጽሐፍ ርዳታ አግኝታለች። ቤተ እስራኤል ከኢትዮጵያ የምትቀድመው መጻሕፍትን በመቀበል እንጂ በእምነት አይደለም። ኢትዮጵያ ላጠናቸው ሃይማኖት አጋዥ የሚሆናት ትምህርት እንጂ አዲስ ሃይማኖት ፈላጊ አልሆነችም ለዚህም ከተቀበለችው ትእዛዝ ማንኛውንም ሳትለውጥ ሕጉን ትእዛዙን ጠብቃ እምልኮቱን ከቀዳማዊ ምኒልክ እስካለንበት ዘመን ድረስ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆና ኖራለች።

ከላይ በዝርዝር የተመለከትናቸው በሌሎች ሀገሮች በግሪክ በላቲን ክርስትናን በተቀበሉ ሀገሮች ሁሉ ይህ አይታወቅም። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ግዝረትን የሚፈጽሙ፣ የማይበሉ እንስሳትና አዕዋፋትን የማይመገቡና፣ ሌሎችን ሥርዓቶች የሚፈጽሙት ከክርስትና ያመጡት ሳይሆን ከኦሪት ልማዶች አያይዘው በመያዛቸው ነው። በቤተክርስቲያን ቀኖና ሕግ ምዕመናንም ልጆቻቸውን ቢያስገርዙም ባያስገርዙም የራሳቸው ፍቃድ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተቻቸው ስጦታዎች ከሚጠቀሱት ውስጥም ጥቂቶቹ፡-

ሀ. ሙሉ ትምህርት

ለ. ፍጹም ቋንቋ ከነፊደሉ

ሐ. ሥነ ጽሑፍ ከነሞያው ከነጠባዩ

መ. ኪነጥበብ በዓይነቱ

ሰ. እምነት ከነፍልስፍናው

ሸ. ታሪካዊና ጥንታዊ ቅርስ

ቀ. አንድነት ከነጀግንነቱ

በ. አገር ከነድንበሩ ከነፍቅሩ

ተ. ስም ከነትርጉሙ ከነምልክቱ

አሁንም ቢሆን ትውልዱ ጀግንነቱን አገር ወዳድነቱን፣ ለታሪክ ለባሕልና ለሃይማኖት ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲያድግ በማስተማርና በማበረታታት ቤተክርስቲያን የበኩሏን እስተዋጽዖ እየተወጣችም የምትገኝ ታላቅ ግምጃ ቤት ናት።

ምዕራፍ አራት

ሕገ ወንጌል

ይህ ዘመን ከክርስቶስ መወለድ እስካለንበት ዘመን የሚያጠቃልል ሲሆን ‹ዘመነ ሥጋዌ›፣ ‹ዘመነ ሐዲስ›፣ ‹የትምህርት ዘመን› በመባልም ይጠራል። በዚህ ዘመን የደጋግ ነገሥታቶችን የቤተክርስቲያን አባቶችን መልካም ሥራና የቤተክርስቲያን ጉዞዋን የምናይበት ክፍል ነው።

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ከዚያም በሕገ ኦሪት ስትመራ እንደኖረች ሁሉ የክርስትና እምነት ከሁሉ አስቀድማ የተቀበለች ሀገር ናት። ከንግሥት ሳባ ጀምሮ በየዘመኑ የነገሡ ኢትየጵያውያን ነገሥታት ከእስራኤል ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበራቸው በየጊዜው ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ አምልኮተ እግዚአብሔርን ፈጽመው ይመለሱ ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት ስምንት ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ዘጠኝ ዓመት /8 ዓ.ኩ - 9 ዓ.ም/ ኢትዮጵያን የመራው ንጉሥ ባዚን ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ የስግደትን ሥርዓት ፈጽሞ የክርስቶስን መወለድ አይቶ ተመለሷል። እንደ አባቶቻችን አገላለጽ እንደታሪክ ምስክርነት ክርስትናን ከተቀበሉ ሀገሮች በቀደምትነት ከሚጠቀሱት ኢትዮጵያ ቀዳማዊ ናት፤ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው የሕገ ኦሪት ሊቅና መምህር የነበረው በጃንደረባው አማካይነት ነው።

ንግሥት ሕንዳኬ /ጌርሻሞት/ ከ 34-42 ዓ.ም.

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በኢትዮጵያ ላይ ነግሣ የነበረችው ንግሥት ሕንደኬ ትባላለች። አገርዋን ኢትዮጵያን በደቡብ አስተዳድራለች፤ ህንዳኬ በዚያን ዘመን ለሴቶች ነገሥታት የሚሰጥ የክብርና የማዕረግ ስም ነው። ሌላው ስሟ ጌርሻሞት ይባላል። ጌርሻሞት ማለት በዕብራይስጥ ጋራሽ /አበረረ/፤ ግሬሽ/ማባረር/፤ ግርሽ/ አባረረች ማለት ነው። ስለዚህ ጌርሻሞት ሞትን ያባረረች ማለት ይሆናል። ሕንዳኬ የሚለው ስመ መንግሥቷ እንደሆነ ይነገራል።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባው ማን ነው?

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያን እንደ እስራኤላውያን ልማድ በየዓመቱ ለበዓለ ፋሲካ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር፤ ጃንደረባው አቤላክ /ባኮስ/ በ 32 ዓ.ም. የፋሲካን በዓል ሊያከብር ሊሰግድና ጸሎት ሊያደርግ ተጓዘ። በዚያን ዘመን ጉዞ ኢየሩሳሌም ለመድረስ 4000 ማይልስ መጓዝን ይጠይቅ ነበር። በዓለ ሃምሳን አክብሮ ወደ አገሩ ሲመለስ የነቢዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብብ ነበር። ኢትዮጵያን መቼም ቢሆን ከእግዚአብሔር መለየት አይወድዱምና የበረሃው ሙቀት ሳያሰቅቀው በሰረገላው ውስጥ ሆኖ የነቢዩን መጽሐፍ ያነብባል። የሚያነብበው የትንቢት ቃል ሊገባው አልቻለም ነበር፤ የተሰወረውን መግለጥ ልማዱ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ወንጌላዊውን ዲያቆን ፊልጶስን ወደ ጃንደረባው ላከለት። የሐዋ፡- 8፤26

ጃንደረባው ባኮስ በሰረገላው ተቀምጦ ድሙጹን ከፍ አድርጎ ያነብብ የነበረው ትንቢተ ኢሳይያስ 53፤7 የተጻፈውን ኃይለ ቃል ነበር። ፊልጶስም ጠጋ ብሎ "በውኑ የምታነብበውን ታስተውለዋለህን?" ሲል ጠየቀው፤ ጃንደረባው ባኮስም በተለመደ ኢትየጵያዊ ትሕትናው "የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይህ ይቻለኛል?" ሲል መለሰለት፤ የፊልጶስን በሥጋ ተራ ደካማ መሆን ሳይንቅ ወደ ሰረገላው እንዲወጣና አብሮት እንዲቀመጥ ጋበዘው።

ዲያቆን ፊልጶስም ከመነሻ እስከ መድረሻ ወንጌል ዘርዝሮ ሰበከለት፤ ጃንደረባውም አመነ፤ ወደ ወንዝ ደርሰው "ነዋ ማይ መኑ ይከልእኒ ተጠምቆ ..... እነሆ ውኃ አለ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማን ነው?" በማለት ፊልጶስን ጠየቀው:: ፊሊጶስም፡- ‹በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል› አለው። ለብዙዎች ለማመን የምታስቸግራቸውን ንጽሕት እምነት ‹ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ› ሲል መሰከረ፤ ፊልጶስም ጃንደረባውን ከኢየሩሳሌም 20 ማይልስ ርቀት በምትገኘው በቤተ ሳሮንና በኬብሮን መካከል ባለው ኮረብታ ስር በሚመነጨው ወንዝ አጠመቀው። ቦታዋም ጋዛ በመባል ትጠራለች። ጃንደረባው ተጠምቆ በ 34 ዓ.ም ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ አስቀድማ ንግስት ሕንዳኬ በኋላም የቤተመንግስቱ ሰዎች ተጠመቁ፤ በሀገሩም ኢትዮጵያ ክርስትናን /ወንጌል/ ሰበከ ለዚህም ማስረጃ የቤተክርሰቲያን ታሪክ አባት የሚባለው አውሳብዮስ "ጃንደረባው ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ" ብሎ ጽፏል። በሌላ በኩል ጃንደረባው ለማስተማሩ ማስረጃ ንግሥት ሕንደኬ /ጌርሻሞት/ የተባለች ንግሥት በስሟ ባስቀረጸችው የወርቅ እና የብር ገንዘብ "ዘሞአት በክርስቶስ" "በክርስቶስ ያሸነፈች" የሚል ጽሑፍ ያለበት ሲሆን በንግሥና ዘውድና በገንዘቧም ላይ የመስቀል ምልክት ነበረበት። ኢትዮጵያ በጃንደረባው አማካይነት ክርስትናን በ 34 ዓ.ም የተቀበለች ብትሆንም በሲኖዶስ ሕግ የጳጳሳት መንበር የተሰጣት በ 328 ዓ.ም. ፍሬምናጦስ የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን በተሰጠው ጊዜ /በአራተኛው ምዕተ ዓመት/ ነው።

የሐዋርያት ስብከት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስትና እምነት ዜና የተሰማውና የተሰበከው በኢትዮጵያ ጃንደረባ መሆኑ ባይካድም ከዚህ በማከታተል ቅዱስ ማቴዎስ፣ በርተሎሜዎስ፣ ናትናኤል፣ ማትያስ፣ ፊልጶስ እና ቶማስ የተባሉት ሐዋርያት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሐዋርያዊ ተልእኮቸውን እንደተወጡና ወንጌል በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እንዳደረጉ የታሪክ ጸሐፊዎች ይናገራሉ።

የፍሬምናጦስ አመጣጥ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ክርስትና በኢትዮጵያ ጃንደረባ አማካይነት በ 34 ዓ.ም. የተቀበለች ብትሆንም በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስነት መንበር ያገኘችው ግን በ 4 ኛው መ/ክ/ዘመን ነው። በአቡነ ሰላማ ፍሬምናጦስ አማካኝነት በ 328 ዓ.ም በ 29 ኛው የግብፅ ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ ሿሚነት በአንብሮተ ዕድ ዲቁና ከዚያም ክህነትና ጵጵስና ተሹሞ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኩሉ ኢትዮጵያ ብለው ሹመው ወደ ኢትዮጵያ ላኩት።

ፍሬምናጦስ በሹመት ምክንያት ከተራዎቹ ምዕምናን አልራቀም ይበልጥ በመቀራረብ በምዕምናን መካከል ተገኝቶ መንፈሳዊና ሥጋዊ ችግራቸውን እየተረዳ ከሱ ጵጵስና ሹመት በፊት የክርስትና እምነት ተቀብለው የቆዩትን አጽናንቷቸዋል። ካመኑት መካከልም ብዙዎቹን የእግዚአብሔርን ልጅነት እንዲያገኙ አድርጓል። ቀንና ሌሊት ጠዋትና ማታ ከምዕመናን መካከል ሳይለይ በምዕመናንን ልብ የተዘራውን ቃለ ሃይማኖት ተግቶ በመጠበቁ "ከሳቴ ብርሃን" /ብርሃንን ገላጭ/ የሆነውን ወንጌል የሚሰብክ ብለውታል። ፍሬምናጦስ በጵጵስና ስያሜውም አባ ሰላማ /የሰላም አባት/ ተብሏል።

ፍሬምናጦስ የተሸከመውን መንፈሳዊ ኃላፊነት በትክክል ለመውጣቱ በኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን የመላ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት መስክረውለታል። በቅዱስነት ደረጃም አስቀምጠውታል፤ በኢትዮጵያም ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን ሠርቶአል። ከሠራቸውም ሥራዎች መካከል፦

- የክርስትና ሃይማኖት እንዲስፋፋ አድርጓል
- በዘመኑ የኢትዮጵያ ግዛት ወደነበሩት ወደ ኑቢያ፣ የመን፣ ሚርዊ አምስት ቆሞሳት በመላክ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰበክ ቤተክርስቲያን እንዲስፋፋ አድርጓል።
- ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከግሪክ ወደ ግእዝ ቋንቋ መልሶ ጽፏል።
- የክህነትና ቁርባን ሥርዓት እንዲጀመር አድርጓል።
- የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍና የማንበብን ዘዴ ያስተማረው እርሱ ነው።
- የመጀመሪያውን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አቋቁሟል
- ማኅበረ ጽዮን ሰማያዊት የምትባለው የመጀመሪያ መንፈሳዊ ማኅበር አቋቁሟል።
- የወንጌል ትምህርት ለሕዝቡ በስፋት የሚያደርሱ፣ የሚያጠምቁና የሚያቆርቡ ካህናትና ዲያቆናትን ሾሟል።

ፍሬምናጦስ እነዚህንና ሌሎችንም መንፈሳዊ ትሩፋቶችን ለቤተክርስቲያን አበርክቶ፣ ሐዋርያዊ ተጋድሎውን ፈጽሞ፣ አርፏል። ቅድስት ቤተክርስቲያንም ለአባ ሰላማ የቅዱስነት መዓርግ ሰጥታ በዓለ ዕረፍቱን ሐምሌ 26 በየዓመቱ ታከብራለች።

አብርሃ ወአጽብሃ /298 - 324/

ኢዛናና ሳይዛና በፍሬምናጦስ በ 330 ዓ.ም. ከተጠመቁ በኋላ አብርሃ ወአጽብሃ ተብለው መጠራት ጀመሩ። እነዚህ ሁለት ነገሥታት ሥልጣነ መንግሥቱን ከእናታቸው ከተረከቡ በኋላ ከአባ ሰላማ ጋር በመተባበር ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን ፈጽመዋል።

አብርሃ ወአጽብሃ ያሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት አክሱም ጽዮን፣ መርጡለማርያም፣ ተድባበ ማርያም፣ ዋሻ ተክለሃይማኖት፣ ጣና ቂርቆስ፣ ሸዋ ጎሐጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን፣ የቅድስት አርሴማ፣ የአቡና ሰላማና በስማቸው የተገደሙ ገዳማት አሉ። ከዚህ ሌላ ስብከተ ወንጌልን በሀገሪቱ ውስጥ አስፋፍተዋል። ለንጉሥ ቆስጠንጢኖስና ለንግሥት ዕሌኒ በጻፉት ደብዳቤ መሠረት በኢየሩሳሌም ያለው ቅዱሳት መካናት ርስታችን እንዲመለስ አድርገዋል።

የአርዮሳዊ ቴዎፍሎስ ተልዕኮ ወደ ኢትዮጵያ

ከታላቁ ቆስጠንጢኖስ በኋላ በቁስጥንጥንያ የነገሠው ኮንስታንዲዮስ በእምነቱ አርዮሳዊ በመሆኑ የአርዮስ ኑፋቄ ቀንደኛ ደጋፊ የነበረውን ጊዮርጊስ ዘቀጰዶቅያን የእስክንድርያ ፓትርያርክ አድርጎ ሾሞት ነበር። በመሆኑም ቀደም ብሎ ቅዱስ አትናቴዎስ የተሾመው ፍሬምናጦስ ወደ አርዮሳዊ ፓትርያርክ መጥቶ ትምህርቱን እንዲያስመረምርና ሹመቱንም እንደገና በካቶሊክ እምነት እንዲያስባርክ ጽኑዕ ምኞት ስለነበረው ለኢትዮጵያ ነገሥታት ቴዎፍሎስ በተባለው ሕንዳዊ ቄስ እጅ ደብዳቤ ላከ፤ የኢትዮጵያ ነገሥታት በጽኑዕ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነት ላይ የታነጹ ስለሆነ አልተቀበሉትም። ቅዱስ አትናቴዎስም በተጋዘበት ቦታ ይህንን ዜና ሲሰማ ለኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ነገሥታት የምስጋና ደብዳቤ እንደጻፉ ይተረካል።

ሁለቱም ነገሥታት ግዛታቸው አስፋፍተው እስከ ኬንያ፣ የመን፣ ሶማሊያንና ሱዳንን አንድ አድርገው ከመግዛታቸው በተጨማሪ በእነዚህ ሀገሮች ሁሉ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርገዋል። ሁለቱም ነገሥታት ከግዛታቸው ስፋት የተነሳ ሕዝባቸውን በቅርብ ለማግኘትና ለማስተዳደር ስለተቸገሩ ዕጣ ተጣጥለው አብርሃ አክሱም ሆኖ ሰሜኑን ሲያስተዳድር፣ አጽብሐ ደግሞ ሸዋ ኤረር ጋራ ላይ ቤተመንግሥቱን አሠርቶ ደቡቡን ክፍል ያስተዳድር ነበር። ሁለቱም ነገሥታት ለ 26 ዓመት አብረው ከገዙ በኋላ አብርሃ ከዚህ ዓለም በመለየቱ አጽብሐ ብቻውን ለተጨማሪ ለ 13 ዓመት ገዝቷል።

በዚህ አካሔድ ንጉሠ ነገሥቱ የቤተክርስቲያን የበላይ ጠባቂ እንዲሆን ተወስኖ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የክርስትና እምነት/ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/ እንዲሆን በ 350 ዓ.ም ተወስኗል። ኢትዮጵያ የክርስቲያን ሀገር ደሴት እንደሆነች በዓለም ታወቀች።

በአጠቃላይ አብርሃና አጽብሐ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅዱስነት ደረጃ ሰጥታቸዋለች። እንደሌሎች ቅዱሳን በስማቸው የታነፁ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን አጽማቸው ባረፈበት ቦታ ይገኛል። ቅድስናቸውን የሚገልጽ ዜና መዋዕልም ተጽፎላቸዋል። የሁለቱም ነገሥታት በዓል በአንድ ላይ ጥቅምት 4 ቀን ይከበራል። የቅዱሳን አባቶቻችን ረድኤት በረከታቸው በእኛ በክርስቲያኑና በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ አድሮብን ይኑር አሜን።

ንጉሥ አልዓሜዳ /480-493/

የዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

እነዚህ ተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ምክንያት የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጉባኤ /በ 443 ዓ.ም/ የአንድ ባሕርይ እምነት በመደገፉና በማስተማሩ ምክንያት ለንጉሡ መርቅያንና በንግሥቲቱ ቡበርክልያ ትእዛዝ በደሴት ጋግራ ውስጥ ታስሮ በመሰቃየት ላይ ሳለ ካረፈ በኋላ የአንድ ባሕርይን እምነት በመከተላቸውና በማስተማራቸው የሁለት ባሕርይ እምነት የሚቀበለው ንጉሥ ከፍ ያለ ስቃይ ስለደረሰባቸው በእምነት መሰሎቻቸው የሆኑ ክርስቲያኖች ወደሚኖሩበት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ በ 480/በ 493/ ዓ.ም. በንጉሥ አልዓሜዳ ዘመነ መንግሥት የሮም ግዛት ከነበሩት ከሶርያና ከቁስጥንጥንያ /ታናሻ E አስያ/ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

የዘጠኙ ቅዱሳን ስማቸው ገዳማቸና የእረፍታቸው ቀናት

ተ.ቁ.	ስም	የመጡበት ሀገር	የመሠረቱት ገዳም	የዕረፍት ቀናቸው
1	አቡነ አሌፍ	ቂሳርያ	ብጎዛን /አሕስ/	መጋቢት 11
2	አቡነ አረጋዊ	ሮም	ደብረዳሞ	ጥቅምት 14 /ዕርገታቸው/
3	አቡነ አፍፄ	ታናሽ እስያ	ዮሐ/የሐ/	ግንቦት 12
4	አቡነ ሊቃኖስ	ቁስጥንጥንያ	ደብረ ቆንጽል	ህዳር 21/28
5	አቡነ ገሪማ	ቁስጥንጥንያ /ሮም/	መደራ	ሰኔ 17
6	አቡነ ይምአታ	ኢጣሊያ	ገርዓልታ	ጥቅምት 23
7	አቡነ ጸንጠሌዎን	ሮም /ቁስጥንጥንያ/	አክሱም አጠገብ /ጸንጠልዎን ገዳም/	ጥቅምት 6
8	አቡነ ጽሕማ	አንጾኪያ /ሶርያ/	ጼዴንያ	ጥር 16
9	አቡነ ጉባ	ኪልቅያ /ግሪክ/	ገርርዓልታ	ግንቦት 29

የተሰዓቱ ቅዱሳን አስተዋጽዖ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን፡-

- በመላው ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ወንጌልን አስፋፍተዋል።
- የምንኩስና ገዳማዊ ሕይወት ሥርዓት በአባ እንጦንስና በአባ መቃርስ ሥርዓት አስፋፍተዋል።
- በስማቸው የሚጠሩትን ሌሎችንም ገዳማት መሥርተዋል
- የአቡነ ሰላማን ፈለግ በመከተል መጻሕፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን፤ መጻሕፍተ ሊቃውንትንና መጻሕፍተ መነኮሳትን ከጽርዕ ቋንቋና ከሱርስት ቋንቋ ወደ ግእዝ መልሰዋል።
- ዘጠኙ ቅዱሳን በመጨረሻ ሐዋርያዊ ተጋድሎአቸውን ያደረጉት ለየስራቸው በገደሙት ገዳም ውስጥ በብሕትውና በመኖር ነበር፤ እኚህ ቅዱሳን በሙሉ መነኮሳት ነበሩ።

የምንኩስና ሕይወት አጀማመር

‹‹መነኮስ›› ማለት ከዓለም፣ ከዘመድ፣ ከሕዝቡ የተለየ መነኩሴ፣ መናኝ፣ በቆቡ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባ፣ ብቻውን የሚኖር፣ ጸዋሚ፣ ተሐራሚ፣ ባተሌ፣ ድንግል የሆነ መንፈሳዊ ሰው ማለት ነው። ገዳማዊ ሕይወት ማለት በሙሉ ጊዜና ሕይወት እግዚአብሔርን ለማገልገል ቤተሰቡንና ዘመድን ሀብትንና ንብረትን እንዲሁም በዚህ ዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር ትቶ በገዳም ተወስኖ መኖር ማለት ነው። በገዳም በተመሰሳይ ዓላማና ሕይወት በአንድነት የሚኖር ማኅበረ መነኮሳት ይባላሉ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን በብሕትውና /በንጽሕና በድንግልና/ መኖር የጀመረው ሔኖክ ሲሆን እንደዚሁም ኤልያስና የክርስቶስ ምላሌ የሆነው ካህኑ መልከጼዴቅ በንጽሕና በቅድስና ተወስነው የኖሩ አባቶች ናቸው። በብሉይ ኪዳን መጨረሻና በሐዲስ ኪዳን መግቢያ ላይም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ከሴት ወገንም ነቢይት ሐና በምንኩስና ሕይወት ያለፉ ናቸው።

በሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኩዳን ባለቤት የሆነው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የብሕትውና ሥርዓት እንዲፈጸመ ቅዱሳን መጻሕፍት ይነግሩናል። ለገዳማዊ ሕይወት ለምንኩስናና ለብሕትውና ጀማሪውና መሪው እርሱ ነው። ማቴ፡-4፤12

በክርስትና ታሪክ ከቅዱሳን ወገን በዘመነ ሐዲስ ምንኩስናን የጀመረው ቅዱስ ጳውሊ ከ 25 ዐ እስከ 356 ዓ.ም. ነው።

ምንኩስና በኢትዮጵያ

ሥርዓተ ምንኩስና በኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት /ተሰዓቱ ቅዱሳን ከመምጣታቸው በፊት/ ኢትዮጵያውያን አበው በምናኔ በበረሃ ይኖሩ እንደነበር ይነገራል።

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አባ ዮሐኒ የተባሉ አባት በትግራይ ተንቤን አውራጃ በሀገረ ሰላም ቀበሌ በአባ አምንዮስ ገዳም በመግባት ከሰው ተለይተው፣ ጨዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ጸበአ አጋንንት ታግሰው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ 6 ዐ ዓመታቸው ወደበሔረ ሕያዋን እንደተወሰዱ ገድላቸው ይናገራል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ሥርዓት ምንኩስና በሁለት መንገድ የተስፋፋና የተጠናቀረ ነው። ይኸውም፡-

1. ከውጭ ወደ ሀገር በገቡ ቅዱሳን
2. ከሀገር ውስጥ በተነሡ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን

1. ከውጭ ሀገር የመጡ ቅዱሳን
   - አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን
   - ተሰዓቱ ቅዱሳን
   - አባ ሊባኖስ በ 486 ዓ.ም.
   - አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ
   - አባ ሐራ ድንግል በ 9 ኛ መቶ ክ/ዘመን
2. ከሀገር ውስጥ የተነሡ
   - አባ ኢየሱስ ሞአ
   - አቡነ ተክለሃይማኖት
   - አቡነ ሚካኤል
   - አቡነ ሀብተማርያም
   - አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ
   - አቡነ አሮን ዘመቁት
   - ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ
   - ቅድስት እምነ ወለተጴጥሮስና ሌሎቹም

ኢትዮጵያ ባፈራቻቸው ቅዱሳንና በመሠረተቻቸው ገዳማት ሀገረቷንና ሃይማኖቷን ከወራሪና ከባዕድ ባሕል ጠብቆ ያቆየው ይኸው የቅዱሳን ጸሎት ነው። ኢትዮጵያ በቅዱሳኖቹ ተጋድሎና መልካም ሥራ ለዓለም የቀረች ቤተመዘክር ሆናለች።

አፄ ካሌብ /467 - 537/

አፄ ካሌብ በነገሠበት ዘመን በ 7 ዐ ዓ.ም በጥሮስ ወረራ ምክንያት ወደ የመን ሀገር ተወስደው የነበሩ አይሁዶች ባሕላቸውን ካስፋፉና ንጉሥ እስከማንገሥ ከደረሱ በኋላ በናግራን የሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ ስሜት ማሳየት ጀመሩ። ፊንሐስ /ዘኡባስ/ የተባለው ምሕረት የሌለው ንጉሥ ብዙ ክርስቲያኖች ላይ መከራ ያጸናባቸው ጀመር። በዚህም መከራ ብዙ ክርስቲያኖች ሲሞቱ ያመለጡትም በቁስጥንጥንያ በእስክንድርያና

በአክሱም ለሚገኙ ክርስቲያኖች ነገሥታት የወገኖቻቸውን ሞት ነገሮአቸው ይህን ድርጊትም በአክሱም ቤተመንግሥትና በምዕምናን ላይ ታላቅ ሐዘን አስከተለ።

ጻድቁ ንጉሥ ካሌብ የመጣለትን የድረሱልኝ የሐዘን ደብዳቤ በመመልከት ከመከራ ሊያድናቸው ‹ክተት ሠራዊት፤ ምታ ነጋሪት› በማለት መርከቦቻቸውን ጭነው /ከ 1 ዐሺ እስከ 12 ዐሺ/ በአዱሊስ የባሕር በር በኩል ወደ የመን ገሰገሱ፤ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት በአባ ጸንጤሌዎን ጉዳም በመጸለይና ከአባ ጸንጤሌዎን ቡራኬ በመቀበል ጦርነቱን አድርጎ ፊንሐስን ከነሠራዊቱ ደመሰሰ፤ አፄ ካሌብም የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን ጠግነው የተረፉትንም ምዕምናን አጽንተው ከ 1 ዐሺ ሰራዊት ጋር የሚጠብቃቸው አብርሃ የሚባል ሰው ሾመውላቸው ወደ አክሱም ተመለሱ። አፄ ካሌብም በጦርነቱ መልስ ብዙም ሳይቆዩ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለቅቀው፣ የነገሡበትን ዘውዳቸውን በጌታ መቃብር በጎልጎታ እንዲቀመጥላቸው ወደ ኢየሩሳሌም በመላክ መንነው፣ ልብሰ ምንኩስና ለብሰው፣ በአባ ጴንጠሌዎን ጉዳም ባለው ዋሻ ውስጥ በመግባት ለ 12 ዓመት በተጋድሎ ከቆዩ በኋላ በ 537 ዓ.ም ግንቦት 2 ዐ ቀን በ 7 ዐ ዓመታቸው ዐረፉ።

የአፄ ገብረመስቀል መነሣት ከ **536** እስከ **55** ዐ

ከአፄ ካሌብ በኋላ ልጃቸው አፄ ገብረመስቀል ነግሠዋል። በዚህ ዘመን ከቀድሞው በበለጠ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዓለም በበለጠ ታውቃለች። በተለይም ከእስክንድርያና ከቁስጥንጥንያ ጋር የጠበቀ ዲኘሎማሲያዊ ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር። ከአፄ ገብረመስቀል ሞት በኋላ በየመን ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ጠፍተዋል ለዚህ ደግሞ ትልቁ ምክንያት የመሐመድ መነሣት ነው።

በአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግሥት የተከናወኑ ተግባራት

- አያሌ ገዳማት መገደም
- የሥነ ጽሑፍ መስፋፋት
- የደብረ ዳሞ ገዳም መሠራት እና የእቡነ አረጋዊ መነሣት
- የቅዱስ ያሬድ መነሣት
- የመሐመድ መነሣት እና ሌሎቹም

የቅዱስ ያሬድ መነሣት

ቅዱስ ያሬድ ሚያዚያ 5 በ 5 ዐ 5 ዓ.ም በአክሱም ከተማ የተወለደ አባቱ አብዮድ /ይስሐቅ/ ሲባል እናቱ ታወክልያ /ክርስቲና/ ትባላለች። በስድስት ዓመቱ ወላጅ አባቱ ስለሞተ እናቱ እንዲያሳድገው እና እንዲያስተምረው ለወንድሟ ለአባ ጌዴዎን ሰጠችው አባ ጌዴዎንም እየረዳውና እያስተማረው ለብዙ ጊዜ ኖረ፤ ነገር ግን ቅዱስ ያሬድ ትምህርት የማይገባው ሆነ በመሆኑም አባ ጌዴዎን በየጊዜው ይገስጸውና ይገርፈው ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ቅዱስ ያሬድ የመምህሩን ተግሳጽ በመስቀቅ ወደ አንድ ጫካ ሔዶ በአንድ ዛፍ ፊት ለፊት ወዳለ ድንጋያማ ስፍራ ሔዶ ተቀመጠ፤ በዚያ በተቀመጠበት ሥፍራ ከፊት ለፊቱ በሚታየው ዛፍ አንድ ትል ወደ ዛፉ ወጥቶ የዛፉን ቅጠል ሊበላ ፈልጎ ስድስት ጊዜ ከወጣ ከወረደ በኋላ በሰባተኛው ወደ ዛፉ ጫፍ ወጥቶ የዛፉን ቅጠል /ፍሬ/ ሲመገብ አየና ተደነቀ ከዚህ በኋላ ትምህርት ቤቱ ተመልሶ መምህሩን ይቅርታ ጠየቀ። መምህሩም ፈቀደለትና ይማር ጀመር፤ እግዚአብሔርም የደረሰበትን መከራና ትዕግሥት ተቀብሎት መንፈሱን ልኮ ልቡናውን አበራለት። ከዚያም በአንድ ቀን 15 ዐ መዝሙር ዳዊትን መጋልየ መጋልይ ዘሰሎሞንን በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍት ተገለጹለትና ፍጹም አሰተዋይ ሆነ። ከዚያም በኋላ ሲመተ ዲቁናን ቀጥሎም ቅስናን ተቀበለ፤ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያም ቤተክርስቲያን በንባብና በለሆሳስ እንጂ ጮሆ በዜማ እግዚአብሔርን ማመስገን አልተለመደም ነበር።

እግዚአብሔር በዜማ መመስገን ፍቃዱ ስለሆነ ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ከመላእክት /ከሃየ አራቱ ካህናተ ሰማይ/ ማኅሌት እየዘመረ ሌሊት ያድርና ጠዋት በሦስት ሰዓት ወደ አክሱም ቤተክርስቲያን በመመለስ ደቀመዛሙርቱን ሲያስተምር ይውል ነበር።

የዜማ መጀመሪያ “ሃሌሉያ ለአብ ሃሌሉያ ለወልድ ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወለዳግም አርኣዮ ለሙሴ ዘከመ ይግበር ግብራ ለደብተራ” የሚል ሲሆን ትርጉሙም “ዓለም ሳይፈጠር ለነበረና ዓለምንም አሳልፎ ለዘለዓለም ለሚኖር ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል። የጽዮን ፈጣሪም እግዚአብሔር አምላክ ለመጀመሪያ ሰማይን ፈጠረ ሁለተኛም ደብተራ ኦሪትን እንዴት አድርጎ መሥራት እንደሚችል ለሙሴ አሳየው ማለት ነው”። ይህች የመጀመሪያ ዜማ /ማኅሌት/ አርያም ብሎ እንደሰየማት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

የቅዱስ ያሬድ ዜማ በዓይነት /በድምጽ/ በሦስት ይከፈላል እነርሱም ግዕዝ፣ ዕዝል እና ዓራራይ ናቸው።

ግዕዝ፡ መጀመሪያ የተገኘ ማለት ነው

ዕዝል፡ ሁለተኛ ሆኖ ከግዕዙ ጋር ተደርቦ /ተጨምሮ/ ታዝሎ የሚዘመር

ዓራራይ፡ የሚያራራ ልብን የሚመስጥ ደስ የሚያሰኝ ማለት ነው።

በምሥጢራዊ አገላለጽ

ግዕዝ፡ ለአብ

ዕዝል፡ ለወልድ

ዓራራይ፡ ለመንፈስቅዱስ ምሳሌ ሆነው ይገኛሉ።

ግንቦት 11 በሚነበበው መጽሐፈ ስንክሣር እንደተጻፈው ቅዱስ ያሬድ በመንፈስቅዱስ እየተመራ ዜማውን ሲያቀነባብር ሦስት አዕዋፍ ከገነት ተልከው መጥተው እንደረዱት ይነገራል፤ ስለአዕዋፋቱ በሊላ አገላለጽ እንደተቀመጠው፡- ‹‹ከዕለታት አንድ ቀን ከኤዶም ገነት በሥላሴ አምሳል ሦስት አዕዋፍ ወደ ቅዱስ ያሬድ መጡ፤ አዕዋፉም ሦስት ዓይነት ቀለም ነበራቸው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ሲሆኑ እነርሱም በግዕዝና በዕዝል በዓራራይ ዜማ እንዲሁም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ።»

በዙኑ፡-22፤28 ላይ እንደተገለጸው የበለዓም አህያ እንደሰው በሰው አንደበት እንደተናገረች ከሦስቱ አዕዋፍ አንዷ፡- ‹‹ያሬድ ሆይ አንተ ብጹዕ ነህ አንተን የተሸከመች ሆድ ብጽዕት ናት› አለችው አዕዋፉም ከዓይኑ እንደተሰወሩ ቅዱስ የሬድ በተመሰጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተነጥቆ በዚያም ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔም መንበር ዙሪያ ቆመው በበገና በመሰንቆ እግዚአብሔርን በማኅሌት በዜማ ሲያመሰግኑት ሰማ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተነጠቀ ማለት ነው። ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱን የዜማ ዓይነቶች ለማጥናት የሚረዱ አሥር የዜማ ምልክቶች /ቅርጾች/ አሉ።

እነርሱም፡

1. ይዘት
2. ድፋት
3. ሒደት
4. ቁርጥ
5. ቅናት
6. ጭረት
7. ርክርክ
8. ደረት

9. አንብር
10. ድርስ

እነዚህ ዓሥሩ የዜማ ምልክቶች ዜማን በቀላሉ ለማጥናት የዜማውን አቅጣጫ ለመለየት ይረዳሉ።

ቅዱስ ያሬድ በተጨማሪም የዜማ ድርሰቱንም በቅደም ተከተል ደርሷል። የደረሳቸው የዜማ መጻሕፍት አምስት ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያን በአገልግሎት እየተጠቀመችበት ትገኛለች። እነዚህም፡-

1. ድጓ
2. ጾመ ድጓ
3. ምዕራፍ
4. ዝማሬ
5. መዋሥዕት ናቸው።

ቅዱስ ያሬድ ከእርሱ በፊት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተወሰነ ደንበኛ የቅኔና የዜማ ትምህርት ስላልነበረ ኩበሉይና ከሐዲስ ከሊቃውንት መጻሕፍት እያውጣጣ ደንበኛ የዜማ ስልት አዘጋጅቷል። የቅዱስ ያሬድ ታሪክና የሠራቸው ሥራዎች /ያበረከታቸው ስጦታዎች/ በዚህ አጭር ጽሑፍ ለማስቀመጥ ባይሞከርም በአጭሩ ለቤተክርስቲያን ካበረከታቸው ሥራዎች በከፊል ስለመላእክት፣ ስለእመቤታችን፣ ነገረ መስቀል፣ ከልደት እስከ ዳግም ምጽአት፣ ስለ ማኅሌት መሣሪያዎች፣ ስለ ቅኔ፣ ስለ ክፍለ ዘመናት የመሳሰሉትን መሠረታዊ የሃይማኖት ቅርሶች መሠረት ጥሎልን ያለፈ ታላቅና ቅዱስ የዜማ አባት ነው።

አፄ ገብረመስቀልና አቡነ አረጋዊ ከቅዱስ ያሬድ ጋር ብዙ ጊዜ አብረው እንደኖሩ ገድለ አቡነ አረጋዊ ይናገራል። ቅዱስ ያሬድ ወደ ሰሜንና ወገል አገሚ በጌምድር እየተዘዋወረ ካስተማረ በኋላ በሰሜን ተራራዎች ስር ካለው ጸለምት በተባለው ዋሻ ውስጥ ገብቶ በጾምና በጸሎት ከቆየ በኋላ በ 571 ዓ.ም ግንቦት 11 ቀን ተሠውሮአል።

የመሐመድ መነሣት

መሐመድ የተወለደው በ 57 ዐ ዓ.ም. ሲሆን በሕፃንነቱ አባቱ ስለሞተበት በ 6 ዓመቱ ወደ አያቶቹ ጋር በመሔድ እንዲያድግ ተደርጎ ሳለ አያቶቹ ሲሞቱ ወደ አጎቱ አቡበከር ሔዶ እንዲያድግ ተደረገ። የ 22 ዓመት ወጣት ሲሆን አቡበከር ወደ አንዲት ከድኟ የምትባል ባለጸጋ ነጋዴ ቤት ተቀጥሮ እንዲሠራ አስገባው፤ ይህች ሴት ሁለት ባል ነበራት በአንድ ወቅት እነዚህ ሁለት ባሎቿ ሞቱባት ያኔ እርሷ የ 45 ዓመት እሱ የ 22 ዓመት ሰው እያለ ነበር። በዚህ ሰዓት መሐመድና ከድኟ ሐዲስ ትዳር ሊጀምሩ በቅተዋል።

መሐመድ የ 4 ዐ ዓመት ሰው ሲሆን የሃይማኖት ሥራውን ሥራ አድርጎ ተነሣ፤ እንዲህ በማለት ‹መልአኩ ገብርኤል /ጅብሪል/ ተገለጸልኝ› እያለ፤ እንደ አርዮስ በግጥምና በንባብ ችሎታው መስበክ ጀመረ፤ ቁርአን አዘጋጅቶ፡- ‹ይህ የእስላም መመሪያ ቅዱስ መጽሐፍ ከሰማይ የተገኘ ነው› ብሎ አዋጅ አስነገረ። ሥራውን የጀመረው በመካ እንደሆነ ይነገራል። በጊዜው የባርያ ሽያጭ ይካሔድ ነበር። እነዚህን ነጋዴዎች በመቃወም ሊሸጡ የመጡ 72 ባሪያዎች ነፃ በማውጣት የእምነቱ ማስፋፊያና መጠቀሚያ አደረጋቸው። በዚህም ምክንያት ቀራይሾች /የመካ ነዋሪዎች በጠላትነት ተነሡበት፤ እርሱንም ተከታዮቹንም ማሳደድ ጀመሩ፤ በዚህም የተነሣ መሐመድ ወደ መዲና ሲሸሽ በ 615 ግማሾቹን ተከታዩቹን “ወደ ሐበሻ ሀገር ብትሔዱ በሥሩ ማንንም የማይበድል ንጉሥ ታገኛላችሁ፤ ያም የፍርድ ሀገር ነው፤ አላህም በዚህ ለእናንተ ዕረፍትን ይሰጣችኋል” በማለት ላካቸው።

መሐመድ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ማወቅ የጀመረው ገና በሕፃንነቱ ነው። የመሐመድ ሞግዚት እመ አይማን የተባለች ኢትዮጵያዊት ነበረች። ባይዳው የተባለው ታሪክ ጸሐፊ በመካ ከተማ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ያለችግር እያካሔዱ ይኖሩ እንደነበር ገልጾአል። መሐመድ ስለኢትዮጵያውያን ንጉሥም ይህን መረጃ ያገኘው አብረውት ከኖሩትና ከቅርብ ከሚያውቋቸው ኢትየጵያውያን ነበር።

ስለዚህም እንግዶችን መቀበል ልማዳቸው የሆኑት ኢትየጵያውያን ነገሥታት የመሐመድ ቤተሰቦችን በስደተኛነት ተቀብለው በሀገራቸው ይኖሩ ዘንድ ፈቀዱላቸው፤ በዚህም የፍቅር አቀባበል ከሰደተኞቹ መካከል ከፊሎቹ ወደ ክርስትና ሲመለሱ የቀሩት ግን በእስልምና እምነታቸው ጸንተዋል። አቡ አላህ ከእስልምና ወደ ክርስትና ለመመለስ የመጀመሪያው ሰው እንደሆነ ይነገርለታል፤ በአንጻሩ ከክርስትና ወደ እስልምና በመግባት ቢላል የመጀመሪያው ሰው ነው። ቢላል ትውልዱ ኢትዮጵያዊ ነው።

እነዚህ ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በፈቀዱት መንገድ /እንድም ወደ ክርስትና ተመልሶ አልያም ባሉበት ጸንተው ተቀመጡ እንጂ ንጉሡን ሰብከው፣ መኳንንቱን ቀይረው የእስላም ንጉሥ አላነገሡም፤ የሰለመ ንጉሥ የተሠራም መስጊድ አልነበረም።

መሐመድ በዘመኑ በመካና በአካባቢዋ የፖለቲካና የበላይነት ከተቀዳጀ በኋላ በዘመኑ ለነበሩ የዓለም ታላላቅ መሪዎች የእስልምናን እምነት እንዲቀበሉና ሕዝቦቻቸው በዚህ እንዲመሩ ለማድረግ ደብዳቤ ጽፏል፤ ለኢትዮጵያ ንጉሥ አርማህ ጽፎለት ነበርና «አምኖ ተቀብሎታል» በማለት አንዳንድ የዓረብ ታሪክ ጸሐፊዎች የፈጠራ ጽሑፎችን ጽፈዋል። በመጨረሻም መሐመድ ከመሞቱ በፊት "ሐበሻን"/ ኢትዮጵያን እንዳትነኩ ብሎ በመናዘዝ በ 63 ዐ ዓ.ም በ 6 ዐ ዓመቱ ሞቶአል። ዛሬ ግን የዛሬዎቹም ሆነ የቀድሞዎቹ አክራሪ እስላሞች ይህንን ቃል ባለማክበር ለክርስትናው ቀንደኛ ጠላት በመሆን እስከ አሁን ድረስ እንቅስቃሴአቸው እንደቀጠለ ነው፤ እግዚአብሔር ሁላችንንም በአንዲቷ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንዲያጸናን የእርሱ ፍቃድ ይሁንልን።

አንበሳ ውድም

ዮዲት ጉዲት /ከ 842 እስከ 88 ዐ/

በአክሱም ዙፋን ከ 822 እስከ 841 ዓ.ም ለ 19 ዓመት ከሁለት ወር የነገሠው የኢትዮጵያ ንጉሥ ደግናቸን የሚባል ነበር፤ ነገር ግን ይህ ንጉሥ ሲሞት አንበሳ ወድም የሚባል ሕፃን ልጅ ነገሠ። የነገሠውም ሕፃን ገና ኃይል ያላበጀ፣ ሥርዓተ መንግሥትን ያላጠና ነበር፤ በዚህም ምክንያት ዮዲት የተባለች ፈላሻ አንበሳ ውድም ሀገርንና ሕዝብን ማስተዳደር አለመቻሉን ሰምታ በሰሜንና በላስታ አውራጃ የሚኖሩትን ፈላሾች ወገኖቿን ይዛ ወደ አክሱም ገሰገሰች፤ የአክሱም መንግሥትና መሳፍንት ሕጻኑ ንጉሣቸውም ከ 841 እስከ 842 ዓ.ም ያህል እንደነገሡ ዮዲትን ሸሽተው ንጉሡን ይዘው ወደሸዋ ሀገር ተሰደዱ።

ከዚህ በኋላ ዮዲት ከ 842 እስከ 88 ዐ በኢትየጵያ ላይ ነግሣ የግፍ ተግባሯን ተያያዘችው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን አፈራረሰች፤ አልፈረስ ያላትን አቃጠለች፤ የታሪክ ቅርስ ሰነዶችን አወደመች። ለምሳሌ፦ በአክሱም የሚገኙትን እንደ ሚካኤል፣ ታዕካ ማርያም፣ ቤተ ሚካኤል፣ ቤተ አሞኒ፣ ቤተ አባ ሳሙኤል፣ ቤተ ማርያም ዘወልደ ነፍስ፣ ቤተ አርባዕቱ እንስሳ፣ ቤተ ጊዮርጊስ፣ አክሱም ጽዮንና ደብረ ወርቅ ማርያምን ወዘተ አቃጠለች። ከዚህ በተጨማሪ በዙሪያው ከክርስትና ዘመንም ሆነ በዘመነ ክርስትና የተሠሩ ሐውልቶችን አፈራረሰች፤ መጻሕፍትን፣ አያሌ የቤተክርስቲያን ንዋየተ ቅድሳትን ደመሰሰች፤ ምዕመናም ካህናትም ከቅዱሳን ሥዕላት ጋር አብረው ተቃጠሉ፤ የተረፉትም ወደ ዝዋይ ሐይቅ ደሴቶች ተሰድደዋል። ከዚህም በኋላ ስለሥራዋ ክፋት ሕዝቡ «ዮዲት» በማለት ፈንታ «ጉዲት» /ጉደኛ ጨካኝ/ ‹‹አስቴር» በማለት ፈንታ «እሳቶ» ብሎ ይጠራት ጀመር።

በዚህም መሠረት ዮዲት ጉዲት 4 ዐ ዓመት ነገሠች፤ የካህናት፣ የዲያቆናት፣ የሕዝበ ክርስቲያን ታላቅ ስደት ተጀመረ። ከ 4 ዐ ዘመን በኋላ ጉዲት ሞተች፤ የተሰደደው ንጉሥ አንበሳ ውድም ነገሠ፤ ሰላምና ጸጥታ ሰፈነ። ካህናትና ዲያቆናት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ አክሱም ተመለሱ፤ ይህን 4 ዐ

የመከራ ዘመን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን «የጨለማው ዘመን» ብለው ይጠሩታል። በዚህ ዘመን የየመንና የኑቢያ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና ተለወጡ።

አንበሳ ውድም /ከ 882 እስከ 9 ዐ 2/

አንበሳ ውድም ወደ ንግሥና ከመጣ በኋላ ከሰይፍ የተረፉ መሳፍንት መኳንንት ከሕዝብ ጋር በመተባበር ክርስትና እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረት ተደረገ። ከብዙ ደብዳቤ መጻጻፍም ክርስትናን የሚያጠናክር አባት እንዲመጣ ብዙ ወርቅና ውድ የሆኑ የስጦታ ዕቃዎችን በማስያዝ መልእክተኛ ወደ ግብፅ ተላከ።

በዚህ ዘመን የእስክንድርያ የጳጳሳት መንበር በግብፅ ሀገር በእስልምና መስፋፋት ምክንያት ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ ተዛውሮ ነበር። በዘመኑ የነበሩት የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ አባ ቆዝሞስ ነበሩ። በእርሳቸው መልካም ፍቃድ አቡነ ጴጥሮስ የተባሉ አባት ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው ተሹመው መጡ፤ ሕዝቡም የሃይማኖት አባት ናፍቆት ነበረበትና ተገቢውን አቀባበል አደረገላቸው። ጳጳሱም ያዘነ የተከዘውን በማጽናናት የፈረሰውን ቤተመቅደስ ከንጉሡ ጋር በመቀናጀት በማስጠገን ላይ እያሉ ንጉሥ አንበሳውድም ለ 2 ዐ ዓመታት እንደነገሠ በጽኑ ሕመም ላይ ስለነበር ጳጳሱን ሥልጣነ መንግሥቱን ለመጀመሪያው ወይስ ለሁለተኛው ልጅ ለየትኛው እንዲሰጥ ሲያማክራቸው ለሁለተኛ ልጁ ሊስጥ እንደሚገባ መከሩት።

ንጉሡ አንበሳ ውድም ሲሞት ትንሹ ልጅ ሥልጣኑን ያዘ፤ በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጅ በነገሠው በወንድሙ በጠላትነት ተነሣበት፤ ትልቁ ልጅ በቁጣ ላይ እያለ አባ ፊቅጦር እና አባ ሚናስ የሚባሉ ሁለት ግብፃዊ መነኮሳት ነበሩ። እነዚህ ሁለት መነኮሳት መንፈሳዊነት ስላልነበራቸው የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ጽሑፍ አስመስለው ደብዳቤ በመጻፍ ለትልቁ ልጅ ሰጡት፤ ይህንን በመያዝ ጀሌውን ይዞ ጦርነት ጀመረ በጦርነቱም ትልቁ ልጅ ድል አደረገ።

በዚህ ጊዜ ትልቁ ልጅ አቡነ ጴጥሮስን ወደ እስር ቤት አጋዛቸው፤ ምክንያቱም ከግብፅ መጣ የተባለው ደብዳቤ አባ ጴጥሮስ ከእስክንድርያ መንበር በቀኖና ያልተሾመ አታላይ መሆኑንና የአባቱን ዙፋን የሚወርስ የበኩ B ር ልጅ ነው የሚል ስለነበር ነው።

አባ ሚናስ በአቡነ ጴጥሮስ ፈንታ ጳጳስ ሆነ፤ አባ ሚናስ ሲሾም ፊቅጦር በአባ ሚናስ ቤት ያለውን የወርቅና የብር የተለያዩ ስጦታ ዘርፎ ጠፍቶአል። ይህ ሁሉ አታላይነት በግብፅ የተሰማው ዘግይቶ ነበር፤ አባ ቆዝሞስም የአባ ሚናስን አታላይነት እንደሰማ ወዲያው አሳሰረው፤ አቡነ ጴጥሮስ ግን በእስር ሳሉ ሞተው ስለነበር መንበሩ ያለጳጳስ ቀረ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለ 84 ዓመታት ያህል /ከ 911 እስከ 995 ዓ.ም/ ያለ መንበረ ጵጵስና ቆይታለች። ከአባ ቆዝሞስ በኋላ የተሾሙት ዐራቱ የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት /አባ መቃርዮስ፣ አባ ቴዎፍሎስ፣ አባ ሚናስ፣ አባ አብርሃም/እስኪያርፉ ድረስ ለኢትዮጵያ ጳጳስ አልተላከም ኢትዮጵያ ይህን ያህል ዘመን ጳጳስ ባለማግኘቷ ብዙ ችግር ደርሶባታል።

ንጉሥ ድልነዓድ ከ 9 ዐ 2 እስከ 912

የቤተክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊና ሊቅ የሆኑት ብላቴን ጌታ ጎሩይ ወልደሥላሴ “ዋዜማ” በተሰኘ መጽሐፋቸው እንደገለጹት ድልነዓድን «ከአንበሳ ውድም ቀጥሎ የነገሠ» ብለውታል። ድልነዓድ በ 1 ዐ ዓመት የንግሥና ዘመኑ ሕዝቡን በተረጋጋ ሁኔታ ለማስተዳደር አልቻለም፤ ይህም የሆነበት ምክንያት በአክሱም መንግሥት ተገዥ የነበሩት ከምስራቅ በኤርትራ ባሕር ዳር የሚገኙት የምጽዋ ዳህላክ ደሴቶች በዓረቦች እጅ መግባትና በእነዚህም ወደቦች ለአክሱም መንግሥት በግብርና በቀረጥ የሚገባውን የንግድ ጥቅም መዘጋት ነበር። የአክሱም መንግሥት ወደቡን በማስጠነቁ በሀብትም በግዛትም መደህየት የተመለከቱና በሰላም ጊዜ እየገበሩ ይኖሩ የነበሩ የአገው የላስታ ነገዶችም አንቀበልም በማለታቸው ለአክሱም መንግሥት መውደቅና ለዛጉዌ/የ/ መንግሥት መነሣትም ምክንያት ሆኗል።

ምዕራፍ አምስት

የዛግዌ ሥርወ መንግሥት

ከመራ ተክለሃይማኖት እስከ ይትባረክ

መራ ተክለሃይማኖት /912 እስከ 925/

ዛግዌ ማለት “ዘአጉየየ” ሲሆን ይኸውም ቃል ጎየ /ሸሸ/ ከሚል የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ይኸውም ያሳደደ/አሳዳጅ ወይም ያባረረ/አባራሪ/ ማለት ነው።

መራ ተክለሃይማኖት በአገውና በላስታ መካከል በሚገኘው ቡግና በተባለው ቦታ ተወለደ፤ አባቱ መርሐ ክርስቶስ እናቱ ሥነ ማርያም፤ ጠቅላላ ዘሮቹ ደግሞ ነገደ ዛግዌ ይባላሉ። ይህም ነገደ ዛጉዌ የተባለበት ምክንያት መራ ተክለሃይማኖት በነገሠ ጊዜ ዛጉዬ በመባል ስመ መንግሥት አድርጎ በመንገሡ ከእርሱ በኋላ ለተነሡ ትውልዶች የነገድ ስም ሆኖአቸዋል።

መራ ተክለሃይማኖት የላስታ ሰው ነው ብንልም የዛግዌ መንግሥት ከንጉሥ ሰሎሞን ሐረግ ጋር የተያየዘ እንደሆነ ይነገራል። ምክንያቱም የላስታ አገው ቀድሞ ነገደ አዱል በመባል መጠሪያ ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ አባቱ ሐዶ ሲመለስ ከ 12 ቱ ነገደ እስራኤል 12 ዐዐዐ የሆኑ የበኩር ልጆቻቸው ከልጁ ምኒልክ ጋር እንዲሔዱ ሰሎሞን ከላካቸው ውስጥ አንዱ የጭፍራ አለቃ ሆኖ የመጣ አዱል ለላስታ ለአገው ለየጁ ለተባለው እና በዙሪያው ለሚኙት ንጉሥ አድርጎ ከነጭፍሮች ሰድዶት ነበርና ነው።

መራ ተክለሃይማኖት በእፄ ድልነዓድ ቤተመንግሥት እጋፋሪ ሆኖ ሲኖር የእፄ ድልነዓድ ልጅ መሶበ ወርቅን እግብቶ ይኖር ነበር፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ድልናኦድ የጦር መሪ አድርገ ሾሞት ስለነበር በእርሱ ላይ ጦርነት ከፍቶ ድልናኦድን ከሥልጣኑ /ከመንግሥት/ አባርሮ የዛግዌን መንግሥት መሠረተ።

የዛግዌ ሥርወ መንግሥት ዋና ከተማ ሮሃ /ቡግና/ ይባላል። ይህም ስም በላሊበላ ዘመነ መንግሥት በንጉሥ ላሊበላ ተሰይሞ እስከአሁን ድረስ ይጠራበታል። በእነዚህ 11 የዛጉዌ ነገሥታት ዘመን ቤተክርስቲያን ከሚጠበቀው በላይ የተራመደችበትን ዘመን ነው መራ ተክለሃይማኖት ቤተመንግሥቱን ከሥራ በኋላ በዮዲት ጉዲት የተቃጠሉትንና የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት ለመሥራት ደክሟል። በዘመኑ የነበሩት ጳጳስ አባ ዳንኤል እንደነበሩ ይነገራል፤ መራ ተክለሃይማኖትም ለ 13 ዓመት የዛጉዌን መንግሥት ከመሠረተና ከመራ በኋላ ዐርፏል ልጁም ጠጠውድም በምትኩ ነግሣ E ል።

በአጠቃላይ የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ለ 333 ዓመታት ኢትዮጵያን ሲያስተዳድራት 11 ነገሥታት ሆነው ነው። እነርሱም፡-

- መራ ተክለሃይማኖት
- ጠጠውድም
- ጃንሥዩም
- ግርማ ሥዩም
- መይራራ
- ሀርበይ
- ይምርሃነክርስቶስ
- ሐርቤ /ጎበረማርያም/
- ላሊበላ
- ነአኩ B ቶ ለአብና
- ይትባረክ ናቸው

ከነዚህ ነገሥታት መካከል የቅድስና መዓርግ/ ማዕረግ ያገኙ አራት ቅዱሳን ነገሥታት የሚባሉት ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ሐርቤይ /ጎበረ ማርያም/፣ ቅዱስ ላሊበላ እና ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ናቸው

ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ /1 ዐ 77 እስከ 1117/

የግርማ ሥዩም ልጅ ነው፤ በታሪክ የታወቀውን፣ በሥራም የተመሰገነውን የቤተ ጉበርኤል ቤተክርስቲያንና ቤተመንግሥቱን ውግራ ሰሂን በተባለው ዋሻ ውስጥ የሠራ ነው። ቅዳሴ ጉበቶ ሲቀድስ ሰማያዊ መና እና ወይን ከነጽዋዕው ወርዶለታል። በነገሠበት ዘመን ሁሉ ከሮማውያንና ከግብፅ ነገሥታት ጋር ይላላክ ስለነበር ብዙ ገጸ በረከት ተልኮለታል። በጥበቡ የተመሰገነ፣ በሥራው ጠንካራና ቆራጥ ከመሆኑም በላይ በሃይማኖት በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ስለነበር የቅዱስነት ስምና ክብር ተሰጥቶታል። መታሰቢያውም በዐረፈበት ቀን በየዓመቱ ጥቅምት 19 ይከበራል። እርሱም እንደአባቶች ሲያርፍ በዙፋኑ ላይ ሀረበይ ተተካ። አጽሙም በዚህ ቤተክርስቲያን የተለየ ቦታ ተሰጥቶት ይገኛል።

ቅዱስ ሐርቤ ወይም ቁሱ ንጉሥ /ጉበረ ማርያም/ ከ 1117 እስከ 1157/

ስመ መንግሥቱ ጉበረማርያም ይባላል። የዛጎ ስዩም ልጅ ነው፤ ለንጉሥ ላሊበላ ወንድሙ ነው። የእናቱ ልጅ በምትሆን እኅቱ ምክር እየተመራ ቅናት ስላደረበት በስህተት ላሊበላን በማስከፋቱ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ተጸጽቶ ፈጣሪውን እንዳያስቀይም ወንድሙን ይቅርታ ጠይቆ በመሪር ሐዘን ንሰሓ ስለገባ ምሕረት አግኝቶ ወደ ቅዱስነት ደረጃ ደርሷል። በዘመኑ ከፈጸማቸው ዋና ዋና ተግባራት አንዱ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እራሷን ለማስቻል ያደረገው ሙከራ የሚጠቀስ ነው። የመንግሥቱ ዘመን 4 ዐ ዓመት ስለነበር በሕይወቱ መንግሥቱን ለወንድሙ ላሊበላ አስተላልፎል፤ አንድ ዓመት ያህል ቆይቶ እንደአባቶቹ ዕድሜን ጠግቦ ዐርፏል። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ይባላል። ግን ታቦት አልተቀረጸለትም፣ በስሙም ቤተክርስቲያን አልተሠራለትም።

ቅዱስ ላሊበላ /ላልይበላል/ ከ 1157 እስከ 1197/

ከዛጉዬ ልጆች በብዙ አህጉር ዝናው የታወቀ ቅዱስ ላሊበላ ነው። አባቱ ዛጎ ሥዩም እናቱ ኬርዎርና ይባላሉ። እናቱ ኬርዎርና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅድስና መዓርግ ተሠጥቷታል። መስከረም 12 ቀን በዓሏ ይከበራል። ቅዱስ ላሊበላ የተወለደው ታኅሣስ 29 ቀን 112 ዐ ዓ.ም ቡግና በተባለው ከላስታ ክፍለ ሀገር ነው። መስቀል ክብራ የተባለችውን ከላስታ ባላባቶች የተወለደችውን አግብቶ ገ/መስቀል መባልን ስመ መንግሥት አድርጎ በ 119 ዐ ዓ.ም ሥርዓተ ንግሥናን ፈጸመ። በአገውኛ ቋንቋ ‹ላል› ማለት ‹ማር› ማለት ሲሆን “ላሊበላ” የተባለው በተወለደ ጊዜ በንቦች ተከቦ ስለተገኘ ነው።

ቅዱስ ላሊበላ ያሠራቸው ውቅር አብያተ ክርስቲያናት 11 ሲሆኑ የቦታው አቀማመጥና የአብያተ ክርስቲያናት አሠራር ምሳሌያዊ ነው፤ የተወሰኑት አብያተ ክርስቲያናት ስለ ሰማያዊቷ ሀገር ምሳሌ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ ለምድራዊቷ ኢየሩሳሌም ምሳሌ ናቸው። እነርሱም፡-

1. ቤተ ጉብርኤል ለመንገደ ሰማይ
2. ቤተ ሊባኖስ የኪሩቤል
3. ቤተ መርቆርዮስ የሲዖል
4. ቤተ አማኑኤል የገነት
5. ቤተ ማርያም የጌቴሰማኒ
6. ቤተ መድኃኔዓለም የደብተራ ኦሪት
7. ቤተ ጎልጎታ የጌታ መቃብር
8. ቤተ ደናግል የእምነትና የፍቅር /የ 36 ቱ ቅዱሳት አንስት/
9. ቤተ መስቀል የቀራንዮ

10. ቤተ ሚካኤል የአዳም መቃብር
11. ቤተ ጊዮርጊስ ዐውደ ፍትሕ /የኖኅ መርከብ/

ከዚህ በተጨማሪ ዋሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን /በዘንዶ የሚጠበቅ/ በጎንደር ዋሻውን አሻሽሎ አንዖታል። በአጠቃላይ ላሊበላ ከቋጥኝ የሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት በመላው ኢትዮጵያ 23 ይደርሳሉ።

በመጨረሻም የሕይወቱ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ የአጎቱን ልጅ ነአኩቶ ለአብን በመንግሥቱ አስቀመጠ። በነገሠ በዓርባ ዓመቱ ሰኔ 12 ቀን ዐረፈ፤ አስክሬኑ ጻድቁ ገብረመንፈስ ቅዱስ በተገኙበት ቤተ ጎልጎታ በተሰኘው ራሱ ባዘጋጀው መቀብር ተቀበረ። ቤተክርስቲያንም ቅዱስነቱን በማረጋገጥ በቅዱስነት ተቀበላዋለች። በተጨማሪ የተወለደበትን ታኅሣስ 29 ቀን በማክበር ላይ ትገኛለች።

ቅዱስ ነአኩ B ቶ ለአብ /1197 - 1235/

ነአኩ B ቶ ለአብ የተባለው እናቱ ምጥ ተይዛ ሳለ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆን ነአኩ B ቶ ሲል በመወለዱ ነው። የላሊበላ ወንድም /የሐርበይ ልጅ/ ነው። እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ድንግል ነው፤ የሰረገላ መንኮራኩር ተሰጥቶት ለመንፈሳዊ ተልዕኮ ይንቀሳቀሳል። ይህ ንጉሥ እንደሌሎች ወንድሞቹ ሁሉ በሥርዓተ እግዚአብሔር የተጠመደ የሃይማኖት ሰው እንደነበር ገድሉ በሰፊው ያትታል። ጾምና ጸሎትን ሲሳዩ አድርጎ በተለይ ዓርብ ዓርብ የጌታውን ስቅለት በማሰብ በቁመቱ ልክ ጉዳጓድ አስቆፍሮ በግራ በቀኝ በፊት በኋላው ጦር በመሰካት ገላውን እንዲወጋው አድርጎ ይሰግድ ነበር። ከነሥጋው ስለተሰወረ ‹ስውሩ ንጉሥ› በመባል መጠሪያ ስም ሆኖት ይኖራል። የአካባቢው ተወላጅ መሃላውን ሲፈጽም ‹ስውሩን!› እያለ መሆኑን በቦታው ሒዶ መረዳት ይቻላል። በግብፅና በኢየሩሳሌም ነግሦ የነበረው ለሡልጣን ሂን በ 1177 ዓ.ም መልእክት በመላክ ርስቱን እንዲጠይቅ ጠየቀ ሱልጣኑ ሀሳቡን አልቀበል ቢለው ለሮም ሊቀጳጳስ እስክንድርያ 3 ኛ ጉዳዩን ገለጠላቸው። ጳጳሱም ከሡልጣኑ ጋር በመነጋገር የዴር ሡልጣንን ርስት ለኢትዮጵያ እንዲመለስላቸው አደረገ። መንግሥቱን 4 ዐ ዓመት በመንፈሳዊ አስተዳደር ከመራ በኋላ ተሸጦ የነበረውን የላሊበላን ልጅ ይትባረክን አስመልሶ በክብር ያሳደገው ስለነበር መንግሥቱን ለእርሱ አስረክቦ ከአምላኩ በደረሰው ጥሪ መሠረት ተሰውሮል። ቤተክርስቲያንም ቅዱስነቱን ተቀብላ ጎዳር 3 ቀን ታከብረዋለች።

የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ነገደ ዛጉዌ ካለፈ በኋላ በዘመኑ ተይዘው እንዳይታሰሩ በመፍራት ዘመናቸውን በሽሽትና በዋሻ ተደብቀው ያሳልፉ የነበሩት የቀዳማዊ ምኒልክ ወገኖች እነዚህ ናቸው፡-

1. ማኅበረ ውድም
2. አግብዓ ጽዮን
3. ጽንፈ አርዕድ
4. ነጋሽ ዞሬ
5. አስፍሐ
6. ያዕቆብ
7. ባሕር አሰግድ
8. አድማስ ሰግድ
9. ይኩኖ አምላክ

ምዕራፍ ስድስት

ከአፄ ይኩኖአምላክ እስከ አፄ ገላውዴዎስ

አፄ ይኩኖ አምላክ /ስመ ክርስትናው ተስፋኢየሱስ /1245 እስከ 126 ዐ/

ይህ ዘመን ከዛግዌ ሥርወ መንግሥት ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የተዘዋወረበት ዘመን ነበር፤ በአባታችን በአቡነ ተክለሃይማኖት ልመናና በአቡነ ኢየሱስ ሞዓ እርዳታ ከንጉሥ ይትባረክ ለአፄ ይኩኖ አምላክ ተመለሰ። አፄ ይኩኖአምላክ ለዚህ ውለታ ከመንግሥቱ ከሦስቱ እጅ አንዱን እጅ የእጨጌነት ማዕረግ መስጠቱን ታሪክ ነገሥት ያስረዳል።

በይኩኖ አምላክ /ተስፋ ኢየሱስ/ ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ጳጳስ አልነበረም። ገድለ ተክለሃይማኖት እንደሚለው አቡነ ተክለሃይማኖት አረማውያንን አስተምረውና አጥምቀው ቀድሰው ለማቁረብ ጽላትና ሚሮን አጥተው ተቸግረው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልዩ አረማዊ ንጉሥ ሞተሎሚ ያረከሰውን ጽላት የሚረከብ ጳጳስ ባለመኖሩ እሳቸው ባርከው እንዲቀድሰብት ከእግዚአብሔር መቀበላቸውን ሲገልጽ “በሊቃነ ጳጳሳት እንደሚሾሙ ሌሎች ጳጳሳት ሳይሆን እንተን ግን እኔ እሾምሃለሁ” አላቸው ይላል። ስለዚህም አፄ ይኩኖአምላክ በዘመኑ ጳጳስ ስላልነበረ ቀብተው ያነገሡት አቡነ ተክለሃይማኖት እንደሆኑ ይነገራል።

በአፄ ይኩኖ አምላክ የነበሩት ጳጳሳትን አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አቡነ ኢየሰስ ሞዓ፣ አባ ጊሩተ አምላክ እና ሌሎችም ቅዱሳን እንደነበሩ ይነገራል።

የአቡነ ኢየሱስ ሞዓ ደቀመዛሙርት

1. አባ ተክለሃይማኖት
2. አባ ጊሩተአምላክ ዘጣና ሐይቅ
3. አባ ዘኢየሱስ

4. አባ በጸሎተ-ሚካኤል
5. አባ አኖሬዎስ ዘደብረ ዳሬት
6. አባ ጉበረ ናዝራዊ
7. አባ ሕዝቅያስ ዘደብረ ቆዘት
8. አባ እስትንፋሰ ክርስቶስ
9. አባ ዮሴፍ እና ሌሎችም

ከእነዚህ ደቀመዛሙርት በተጋድሎ ከጸኑት ቅዱሳን መካከል አቡነ ተክለሃይማኖት አንዱ ናቸው።

አቡነ ተክለሃይማኖት ሀገራቸው ሸዋ ቡልጋ ጽላልሽ ሲሆን አባታቸው ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእነረያ ሲባሉ የካህን ልጅ ናቸው። በተወለዱ ጊዜ ብርሃን ሲወርድ በ 3 ኛው ቀን አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስቅዱስ ብለው አመስግነዋል። መጋቢት 24 ቀን ተፀንሰው በታኅሣስ 24 ቀን 1167 ዓ.ም ተወልደው ፍሰሐ ጽዮን ብለው ስም አውጥተውላቸዋል።

አቡነ ተክለሃይማኖት በልጅነታቸው ጸጋ መንፈስቅዱስ ያደረባቸው ታላቅ ሰው ስለነበሩ በንጽሕናና በጸሎት ወንጌልን በመስበክ ሀገራቸውንና ቤተክርስቲያንን በሚገባ አገልግለዋል። በዚህ አገልግሎታቸውም ለ 7 ዓመት ቆመው ሲጸልዩ እግራቸው በመቆረጡ በምትኩ 7 ክንፍ እግዚአብሔር አድሎአቸዋል፤ ጻድቁም አገልግሎታቸውን ፈጽመው በነሐሴ 24 በ 99 ዓመታቸው ዐርፈው በደብረ ሊባኖስ ተቀብረዋል። አቡነ ተክለሃይማኖት ባህታዊ ናቸው፤ ንጽሕናን ጠብቀው ከዓለም ርቀው በአንድ ዋሻ ተወስነው በቅድስና አሸብርቀው የተባህትዎን ሥርዓት ፈጽመዋል። በዚህ ተጋድሎአቸውም ብዙ ደቀመዛሙርት አፍርተዋል እነርሱም፡-

- አቡነ ፊልጶስ ዘደብረ ሊባኖስ ወእጨጌ
- አባ አኖሬዎስ ዘወግዳ (ታናሹ)
- አባ ኢዮስያስ ዘወለም /ዘወንገጃ/
- አባ ዮሴፍ ዘአናርያ /ሊሙ/
- አባ ታዴዎስ ዘጽላልሽ
- አባ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ /አሰቦት/ ሌሎች

ቤተክርስቲያን እኚህን ታላቅ አባት ቅዱስ ብላ ቤተክርስቲያን ሠርታ፣ ታቦት ቀርጻ በዓላቸውን በደመቀ ሁኔታ ታከብራለች።

አፄ ዓምደ ጽዮን /1297 እስከ 1327/

በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ ነበሩ፤ በዚህ ወቅት የደብረ ሊባኖስ እጨጌ አቡነ ፊልጶስ የነበሩ ሲሆን ረድአቸውም/ ረዳታቸውም አኖሬዎስ ዘደጀን ይባላሉ። የአፄ ዓምደጽዮን ዘመነ መንግሥት በብጥብጥና በጦርነቶች የተሞላ እንደነበር ንጉሡም የአባቱን ሚስት እንዳገባና በዚህ የቤተክርስቲያን አባቶች እጨጌ ፊልጶስና 82 መነኮሳት እንደገሠጹትና በዚህ የተነሣ እነርሱን ወደ እስር ቤት እንዳጋዛቸው ታሪክ ይነገራል። ነገር ግን ንጉሡ ኃጢአት መሥራቱን እንዳወቀና በንሰሓም በመመለሱ ቤተክርስቲያን ደስ አላት። ከዚህ የኃጢአት ሥራ ከተመለሰ በኋላም ለሀገሪቱና ለቤተክርስቲያን ታላቅ ሥራ ሠርቷል ለምሳሌም፡-

አያሌ የውጭ ሀገር የታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲተረጎሙ ያደረገ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ መጽሐፈ ግንዘት፣ ውዳሴ ማርያም፣ ግብረ ሕማማት እና ሌሎችም ይገኙበታል። በሀገር ውስጥ በተነሡ ጸሐፍያን የተጻፉ ክብረ ነገሥት፣ ታሪከ ነገሥት /ዘአክሱም/ እና ሌሎችም መጻሕፍት በዘመኑ የተጻፉ ናቸው። እነዚህንና ሌሎችን ሥራዎች በመሥራት አፄ ዓምደጽዮን ይታወቃል።

አፄ ሰይፈ አርዕድ 1327 እስከ 1355

አፄ ሰይፈ አርዕድ በነገሡ ዘመን በግብፅ ንጉሥ አዛኝነት የግብፅ ጳጳስ ታስረው ስለነበር እርሳቸውን ለማስፈታት ወደ ግብፅ እንደዘመቱና በዘመቻውም የግብፁ ከሊፋ ተሸንፎ ለኢትዮጵያዊው ንጉሥ የይቅርታ ደብዳቤና ገጸበረከትም እንደላከላቸው ይነገራል። አፄ ሰይፈ አርእድ ሊቀጳጳሱን አባ ማርቆስን አስፈትተው የተሰጣቸውንም ገጸ በረከት በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በመታሰቢያነት እንዲቀመጥላቸው በመላክ ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

በመጽሐፈ ስንክሳር /ጥቅምት 19 የሚነበበው/ ይህ ሡልጣን ሊቀ ጳጳሱን ካሰረ በኋላ ለአፄ ሰይፈአርዕድ የማስፈራሪያ መልዕክት እንደላከና አፄ ሰይፈአርዕድም ሊቀጳጳሱን እንዲፈቱ ማድረጋቸውን ከመግለጽ ውጭ ስለአጼ ሰይፈ አርዕድ ወደ ግብፅ መዝመት አልገለጸም። በአፄ ሰይፈአርዕድ ዘመነ መንግሥት የተሠሩ ብዙ አድባራት ሲኖሩ ከእነዚህም ውስጥ፦ ደብረ ታቦር ኢየሱስ፣ በጐንደር እና የምናዝሮ ተክለሃይማኖት /በሰሜን ጎንደር/ ናቸው።

በእኚህ ንጉሥ ዘመን የነበሩት ጻድቅ አቡነ ቶማስ ይባላሉ።

አፄ ዳዊት /ከ 1365 እስከ 1395/

አጼ ዳዊት ከአባታቸው ከሰይፈ አርዕድ ቀጥለው የነገሡ ንጉሥ ናቸው፤ በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ብዙ የተከናወኑ ተግባሮች ቢኖሩም የቅዱስ ግማደ መስቀል አመጣጥ የሚደንቅ ነው።

የግማደ መስቀል አመጣጥ

አጼ ዳዊት ለብዙ ዓመታት በኢትዮጵያ የነገሡ ሲሆን በዘመናቸውም በግብፅ በሰላም ተፈቶ የነበረው ክርስቲያኖች የማንገላታት እንቅስቃሴ እንደገና አገርሽቷል። በአብያተ ክርስቲያናትም ላይ መከራ አጸኦባቸው፣ ሊቃነጳጳሳቱም ታሰሩ። ክርስቲያኖቹም ተመካክረው ወደ አፄ ዳዊት የአድኑን ጥሪ አስተላልፈዋል።

አፄ ዳዊት ክርስቲያኖችን ለመታደግ ወደ ግብፅ ዘመቱ፤ ካርቱም እንደደረሱ፦ ‹ግብፅ ድረስ ምን ያደክመኛል?› በማለት ካርቱም ላይ የዓባይን ውኃ ገድበው ወደ ሱዳን በረሃ እንዲፈስ አደረጉት ግብፃውያኑም አፄ ዳዊት በወሰዱት እርምጃ ተደናግጠው ለአጼ ዳዊት 12 ዐዐዐ /መቶ ሃያ ሺህ/ ወቄት የሚሆን ወርቅ እጅ መንሻ ላኩ። አጼ ዳዊትም የተሰጣቸውን እጅ መንሻ ገጸ በረከት ከምንም ሳይቆጥሩ በመታሰቢያነት በዚያው በእስክንድርያ ቤተክርስቲያን እንዲቀመጥላቸው በመስጠትና በወርቁም ምትክ የጌታ መስቀል እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ግብፃውያኖቹ በዓባይ ውኃ ሕይወታቸው ከምታልፍ ንግሥት ዕሌኒ ከተቀበረበት አስቆፍራ ያስወጣችውን የጌታችንን ቅዱስ መስቀል፣ ወንጌላዊው ሉቃስ የሳለውን ምስለ ፍቁር ወልዳ፣ የጌታ አክሊለ ሶክ በሊቀጳጳሳቱ አስይዘው አጼ ዳዊት ያሉበት ድረስ ላኩላቸው።

አፄ ዳዊት መስቀሉን መስከረም 1ዐ ቀን በ 1395 ዓ.ም ተረከቡ። መስቀሉን ይዘው በጉዞ ላይ ሳሉም መስከረም 21 ቀን 1395 ዓ.ም በሕልማቸው “ይነብር መስቀልየ በዲበ መስቀል” . . . ‹መስቀሉ በመስቀል ላይ ይቀመጣል› የሚል ራእይ ታያቸው።

አፄ ዳዊት ቅዱስ መስቀሉን አስይዘው ወደ ምድረ ኢትዮጵያ ጉዞአቸውን እያደረጉ ሳለ ምንም ሳይታመሙ በድንገት ጥቅምት 2 1395 ዓ.ም መስቀሉን በተረከቡ በ 29 ኛው ቀን ‹ስናር› ከሚባል ቦታ ሲደርሱ ዐረፉ፤ ቅዱስ መስቀሉም በግብፃውያን ጳጳሳት እጅ በአደራ ለብዙ ዘመናት በሱዳን ቆይቶአል።

ከአፄ ዳዊት ቀጥለው የነገሡት ልጆቻቸው ሲሆኑ በቅደም ተከተል እንደነገሡ ታሪክ ነገሥት መዝግቦ አስቀምጦታል። ነገር ግን እነዚህ ነገሥታት በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊም ደካሞች ቢሆኑም ከእነዚህ ውስጥ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊ ሕይወት አፄ ዘርዓያዕቆብ በኢትዮጵያ ታሪክና ቤተክርስቲያን ታሪክና ቤተክርስቲያን ትልቅ ስፍራ ይዞ ይገኛል። በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የነበሩት ጳድቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይባላሉ።

አፄ ዘርዓያዕቆብ ከ **1437** እስከ **1468**

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንድታድግና እንድትስፋፋ የደከመ ታላቅ ንጉሥ ነው። የተወለደው 1391 ዓ.ም ነው። አባቱ ንጉሥ ዳዊት እናቱ እቴጌ እግዚአ ክብራ ይባላሉ። የአባቱ የመጨረሻ ልጅ ነው፤ በልጅነቱ ከቤተመንግሥት የሥልጣን ሹክቻ ለማራቅ እናቱ እግዝአ ክብራ ወደ ደብረ ቢዛን አባ ፊልጶስ ጋር ላከችውና ዮስጢኖስ የተባለ መምህር ጋር ትምህርቱን ተምሮአል።

የአፄ ዘርዓያዕቆብ ሁሉም ወንድሞች በየተራ ነግሠው እስኪያልፉ ድረስ በደብረ ዓባይ እንደቆየ ይነገራል። በመጨረሻም የቀረ እርሱ ስለነበረ ሠራዊቱ ከተደበቀበት አስሶ አምጥቶ በኃይል አነገሠው። አፄ ዘርዓያዕቆብ ሥልጣኑን ሲይዝ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ተልዕኮ የሚጠይቃት ወቅት ነበር። በንጉሡም ዘንድ የተሠሩ ሥራዎች በረከቶች ናቸው። እነዚህም፡-

- ጳጳሳትን ማስመጣት አቡነ ሚካኤል፣ አቡነ ገብርኤል፣ ኤጲስ ቆጶስ አባ ዮሐንስ
- በሰንበት ምክንያት የተነሣው ክርክር መቋጫ እንዲኖረው ማድረግ
- አምልኮ ጣዖታትን እንዲወገዱ ማድረግ
- የደቂቀ እስጢፋ ምንፍቅና መወገድ
- ትምህርተ ወንጌል የሥነጽሑፍ መስፋፋትና የምንከ B ስና ሕይወት ከፍተኛ ደረጃ መድረስ
- ትምህርተ ወንጌል የተስፋፋውና የምንከ B ስና ሕይወት ያደገው በቤተ ኤዎስጣቴዎስ ደቀመዛሙርት አማካይነት በቤተ ተክለሃይማኖት ገዳማት እንዲስፋፋ አድርገዋል፤ በዚህም ዘመን ተአምረ ማርያም እንዲነበብና ሕዝቡ በዕለተ ሰንበት ቅዳሴ እንዲያስቀድስና እንዲሰማ አድርገዋል።

የቅዱስ መስቀል አመጣጥና ፍጻሜ ያገኘው በአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው፤ በአፄ ዳዊት በድንገት መሞት ከፍጻሜ ሳይደርስ የቀረውን የቅዱስ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት እንዲሔዱ ያደረጋቸው በሕልማቸው “እንበር መስቀልየ በዲበ መስቀል” …. ‹መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አኑር› የሚል ራእይ ይታያቸው ስለነበር ቅዱስ መስቀሉን በመስቀለኛ ቦታ ላይ ለማስቀመጥ ወደ ሱዳን አምርተው ቅዱስ መስቀሉን መስከረም 21 ቀን በ 1443 ዓ.ም ተረከቡ። ኢትዮጵያ እንደደረሱም በብዙ ቦታዎች ላይ በማስቀመጥ መስቀለኛ ቦታዎች በማፈላለግ ሳሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዛሬ በሚገኝበት በአምባሰል አውራጃ ግሸን ደብረ ከርቤ በሚባለው ተራራማ /መስቀልኛ/ ሥፍራ አኖሩት።

በግብፅ ይኖሩ የነበሩት ክርስቲያኖችንም ከአሕዛብ እጅ ግፍ ማስለቃቃቸው ይነገራል፡ ለዚህም በግብፅ ሀገር የምትገኝ ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በዘመኑ በኃይል አይለው የነበሩ እስላሞች አቃጠሏት። በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖች ወደ አፄ ዘርዓያዕቆብ ንጉሥ የድረሱልኝ ጥሪ

አስተላለፉ አፄ ዘርዓያዕቆብ ይህን በሰሙ ጊዜ ሠራዊት አስከትለው ወደ ግብፅ ወርደው አስላሞች ገደሏቸው። ከሰይፍ የተረፉ ክርስቲያኖችንም አጽናንተው የፈረሱትን ሕንፃ አብያተ ቤተክርስቲያናትንም አሠርተው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

የአፄ ዘርዓ ያዕቆብም ዘመነ መንግሥት ሥነ ጽሑፍ የተስፋፋበት ዘመን ነው ስንል ንጉሡ ራሳቸውም ብዙ መጻሕፍትን ሰለጻፉ ጭምር ነው እነርሱም፡-

1. እግዚአብሔር ነገሠ /ለቅዱሳን ለሰማዕታት የተሰጠ ሰላምታ/
2. ጦማረ ትስብዕት / ስለ ትስብዕትና ስለ ጠንቋዮች የሚናገር/
3. መጽሐፈ ባሕርይ /ስለ ኦዛዜ የሚናገር/
4. መጽሐፈ ብርሃን/ ስለሰንበታት አከባበርና አምልኮ ጣዖት እንዲጠፋ የሚናገር/
5. ተአክሶ ምሥጢር / ስለ ቅዱስ ቁርባን የሚናገር/ እና ሌሎችን መጻሕፍት እንደጻፉ/ እንደደረሱ ይነገራል።

ከዚህ በተጨማሪ አቡነ ዘበሰማያት ከሚባለው የጸሎት ክፍል ጋር በሰላመ ቅዱስ ጉበርኤል..... የሚባለውን ጸሎት አብሮ እንዲጸለይ አድርገዋል። 675 ሕንፃ ቤተክርስቲያን አሳንፀዋል። አፄ ዘርዓያዕቆብ እነዚህንና ሌሎችንም ሥራዎች ሠርተው ጳግሜ 3 ቀን ዐረፉ። በደብረብርሃን ሥላሴ በየዓመቱ ጳጉሜ 3 ቀን የዕረፍታቸው ቀን በቅዳሴ ይታሰባል።

አፄ ልብነ ድንግል ከ **15** ዐዐ እስከ **153** ዐ

አፄ ልብነ ድንግል የአፄ ናኦድ ልጅ እና እንደአባታቸው መንፈሳዊ ትምህርት የተማሩና የቤተክርስቲያን ሥነ ሥርዓት የሚያውቁ ንጉሥ ናቸው። አፄ ልብነ ድንግል ስመ መንግሥታቸው ‹ወናግሰገድ› ተብሎ ይታወቃል። ‹ወናግሰገድ› ማለት በሐረርጌና በውጋዴን ቋንቋ ‹አንበሳ› ማለት ነው። ትርጉሙም “አንበሳን የሚያሰግድ” ማለት ነው። በዘመኑ የግራኝ መሐመድ ጦርነት ተነሥቶአል።

ግራኝ መሐመድ መነሣት

ግራኝ መሐመድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠላቶች ከሆኑት መካከል አንዱ ነው፤ ግራኝ መሐመድ የተነሣው ልብነ ድንግል በነገሠ በ 15 ኛ ዓመት፤ የትውልድ ሀገሩም በአባቱ የሶማሌ ተወላጅ በእናቱ ሐረርጌ ካቀኑት አስላሞች ወገን ኤጋዴን ውስጥ ሁባት በተባለች ቦታ ነው። ግራኝ መሐመድ ሙሉ ስሙ ኢብን ኢብራሂም አልቃዚ በመባል ይታወቃል፤ በኢትዮጵያውያን ግራኝ አሕመድ /መሐመድ/ ተብሎ ይጠራል።

በዚህም ዘመን በኢትዮጵያ የነበረውን ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ብንመለከት የቱርክ አስላሞች ከዓረብ አስላሞች ጋር ኃይላቸውን አስተባብረው የወረራ ተግባራቸውን በማስፋፋት መላዋ ሶሜን አፍሪካና ሌሎች አገሮች ጭምር በአስልምና ተወረሩ፤ ይህ ሁሉ ሲሆን የክርስቲያን ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ አልተደፈረችም ነበር። ነገር ግን ግራኝ መሐመድ በስመ አስላም ከቱርክ ባለሥልጣናት ጋር በድብቅ በመላላክ ክርስቲያኑን ሕዝብ በማረድና ሀገሪቱን ለቱርክ ለማስረከብ ተነሳሳ። ግራኝ መሐመድ በቱርክና በዓረቦች የሚታገዝ ሠራዊት የተደራጀለት ሲሆን የጦር ሠራዊት መሪ የነበረው ማፋዱ የሚባል ነበር።

ግራኝ መሐመድ በሀገሪቱ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናትን በሙሉ እንዲፈራርሱና እንዲቃጠሉ አድርጓል። ከእነዚህም ውስጥ 4 ዐ በዋነኝነት የሚቆጠሩ አድባራትና ገዳማት ናቸው፤ እነዚህም የወረኢሉ መካነ ሥላሴ፣ ደብረሊባኖስ፣ ዝቋላ አቡነ ገብረመንፈስቅዱስ፣ የደብረ ብርሃን ሥላሴ፣ የገነተ ጊዮርጊስ፣ የወልደ ነጎድጓድ፣ የአትጸነስ ማርያም፣ የምስለለ ማርያም፣ የኤነድሮስ ማርያም፣ የታዕካ መንግሥት የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣

የመርጡለማርያም ወዘተ . . . ካህናቱና መነኮሳቱ ገዳማቱ ሲቃጠሉ አብረው በእሳት ተቃጥለዋል። የሃይማኖት የታሪክ መጻሕፍት የእሳት ራት ሆነዋል። ከሰይፍ የተረፉ ምዕምናን እየተገደዱ የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ተደርገዋል፤ ግራኝ መሐመድ በቤተክርስቲያን ላይ ያደረሰው ጉዳት፡-

1. የቤተክህነት የሙያ ደረጃ ዝቅ ማድረግ
2. ያለካህን ፈቃድ ማግባት /ያለተክሊል መጋባት/
3. በሆነው ባልሆነው ሚስት ከባል ባል ከሚስት መፋታት
4. ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች መውለድ
5. ሥርዓተ ምሥጢራትን ዝቅ ማድረግ፤ ለምሳሌ፡- ንሰሓ ቁርባንን እንዲረሱ ማድረግ
6. የቦታዎች ስም መፋለስ
7. ርጥብ /ጥሬ/ ሥጋ መብላት እና ሌሎቹም ናቸው

በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን የነበሩት ጻድቅ አባ ተክለአልፋ ይባላሉ፤ የድሀ እንባ ተብለው ይጠሩ ነበር። ከዐፄ ልብነ ድንግል በኋላ የነገሡት ልጃቸው አፄ ገላውዴዎስ ናቸው።

አፄ ገላውዴዎስ ከ **153** ዐ እስከ **1549**

አፄ ገላውዴዎስ ስመ መንግሥታቸው አጽናፍ ሰገድ በመባል ይታወቃሉ፤ በኢትዮጵያው ታሪክ በቅድስና ማዕረግ የሚከበሩና ከግራኝ ሠራዊት ጋር በተደረገው ውጊያ በሰማዕትነት ያለፉ አባት ናቸው፤ በዚህም የተነሣ የአንጾኪያው ሰማዕት ተብሏል።

በልጅነት ዘመናቸው የጦር መላና መንፈሳዊ ትምህርት በሚገባ የተማሩ ታላቅ ንጉሥ ናቸው። መንፈሳዊ ትምህርታቸውን የተማሩት በደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ነው። አፄ ገላውዴዎስ በወቅቱ ጳጳስ ስላልነበረ በደብረ ዳሞ ንቡረ እድ በአባ ተርቢኖስ እጅ ሥርዓተ መንግሥታቸውን ፈጽመዋል። የመጀመሪያ ሥራቸው ያደረጉት ግራኝ መሐመድን ከሰሜን ኢትዮጵያ ሙሉ ለሙሉ ማባረር ነበር። በመቀጠልም ከፖርቹጊዝ ጦር ጋር አንድ በመሆን የካቲት 21 ቀን 1542 ዓ.ም ጦርነት ተደርጎ ግራኝ ተገደለ፤ በግራኝ መገደል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና ምዕምናን ዕረፍት አገኙ።

አስቀድሞ አፄ ገላውዴዎስ ወደ ጦርነት ከመጓዛቸው በፊት ለጎጃም አድባራት በጸሎታቸው አስቡኝ እያሉ መልእክት ሲልኩም ነበር፤ በዚህ ምክንያትም ግራኝን ድል ካደረጉ በኋላ የግራኝ ካባውን ለመርጡለማርያም ረጅም የሆነውን የብር ሜጦውን ደግም ለደብረ ጽሞና ጌዳም ሰጥተዋል።

በዚህ ዘመነ መንግሥት የነበሩት ጻድቅ አቡነ እጨጌ ዕንባቆም ይባላሉ እጨጌ እንባቆም የመናዊና የአሕዛብ እምነት ተከታይ የነበረና በኋላም በክርስቶስ አምላክነት አምኖና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተከታይ በመሆን መጽሐፈ ቄደርን በመድረስና ወደ እስልምና የገባውን ክርስቲያን ሁሉ መጽሐፈ ቄደርን እየደገሙ ጠበል እንዲረጭና ወደ ሃይማኖቱ እንዲመለስ አድርገዋል።

የካቶሊካውያን አመጣጥ

ካቶሊኮች የቤተክርስቲያን ጠላቶች ብለን ከምንጠራቸው መካከል ሲሆኑ አነሣሣቸው እንደሚከተለው ነው። ግራኝ መሐመድ በተነሣበት ዘመን አፄ ልብነ ድንግልና ልጃቸው /አፄ ገላውዴዎስ/ የግራኝ መሐመድን ሠራዊት በጦርነት መቋቋም ሲያቅታቸው አፄ ገላውዴዎስ ከፖርቹጋል 400 የሚሆን ሠራዊት እንዲመጣላቸው በጠየቁት መሠረት ሠራዊት ተልኮላቸዋል። ከዚህ በኋላ የፖርቹጋልና የኢትዮጵያ ጦር በመተባበር ግራኝ መሐመድን ድል አደረጉ። ከድሉ በኋላ የፖርቹጋል ሠራዊት ብዙዎቹ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ጥቂቶቹ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ቀርተዋል። ከቀሩት

መካከል ቤርሙዴዝ የሚባል መናፍቅ ለአፄ ገላውዴዎስ እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው፡- ‹‹ከአባትዎ ከአፄ ልብነድንግል ጋር የኢትዮጵያ እኩሌታዋ ለፖርቹጋል ልትሆን፣ የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥር እንድትሆን፣ እኔም በኢትዮጵያ የሮማ የመጀመሪያ ፖፖ (አቡን) ልባል ውል ነበረንና ፊርሙልኝ›› አላቸው።

አፄ ገላውዴዎስም፡- ‹‹ይህ የምትለኝ አይገባኝም፤ አልቀበለውም! ላደረጋችሁልኝ ውለታ ዋጋችሁን በብር፣ በወርቅ እንከፍላችኋላን፤ ከአናንተ መሐል ኢትዮጵያን የወደደ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መኖር ይችላል፤ መኖር ያልፈለገ ዋጋውን እየተቀበለ መሄድ ይችላል፤ ከእሁን በኋላ በሀገሬ የሌላ ሀገር ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) ተሰቅሎ ማየት አልፈልግም›› የሚል መልስ ሰጡ።

ቤርሙዴዝ በዚህ ባለመስማማቱ ወደ እስር ቤት ተጣለ። በእስር ቤት እያለ አማላጅ ልኮ ተፈታ። በንዴትም ወደ ሀገሩ ተመልሶ የሆነውን ሁሉ ለፖርቹጋል መንግሥትና ለቫቲካን ቤተክህነት አቀረበ። እነርሱም ተወያይተው ሌሎች ተጨማሪ ሚሲዩናውያንን ቀሚስ አልብሰው፣ ቆብ አስደፍተው፣ መጽሐፍ ቅዱስንና መስቀል አስይዘው በመላክ በክፉ ወሬ መንግሥትን ከሕዝብ፣ መኳንንቱን ከመሳፍንቱ፣ የእጅ ባለሞያዎች ከሕዝቡ ጋር አጣሉት። በዚህም 8 ሺህ ሕዝብ አንዳለቁ ይነገራል። እነርሱም በዚህ አጋጣሚ ውስጥ ውስጡን የምናፍቅና የካቶሊክን የሁለት ባሕርይ ትምህርት ያስተምሩ ነበር። ከአፄ ገላውዴዎስ የንግሥና ዘመን በኋላም በተከታታይ በነገሡት በአፄ ሚናስ፣ በአፄ ያዕቆብ፣ በአፄ ዘድንግል ዘመን ይህ የምንፍቅና (የክህደት) ትምህርት በሀገራችን ኢትዮጵያ ተስፋፍቶአል።

አፄ ሱስንዮስ **(1597-1626)** *ሥልጣን ሰገድ*

አፄ ሱስንዮስ ሥልጣኑን የጨበጡት በመፈንቅለ መንግሥት (በጦርነት) አፄ ያዕቆብን ወግተው ነው። ወዲያው ሳይውል ሳያድር ጎጃም ቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በመሐድ «ሥልጣን ሰገድ» ተብለው ነገሡ። አፄ ሱስንዮስ ከደብረ ታቦር ጋር 20 የሚሆን ከተማ ቆርቁረዋል። ዋና ከተማቸውም ደንቀዝ ይባላል።

በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት የተፈጸሙ ተግባራት

- በካቶሊካውያን ሼራ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የእርስ በእርስ ግጭት እንዲጀምር ማድረግ

የአፄ ሱስንዮስ በንሰሓ *መመለስና* አንደበት *መ*ከፈት

- የካቶሊኮች ሃይማኖት በኢትዮጵያ መስፋፋት ተከትሎ በቀደምት ነገሥታት መሐል ጉበተው ትምህርታቸውን ቢያስፋፉም አጥጋቢ ውጤት ስላላገኙ ጴጥሮስ ፖኤዝ የሚባል ሰው ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በማስመሰልና በዘዴ ንጉሥ ሱስንዮስን አታልሎ በመስበክ የካቶሊክን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን አሳወጀ።
- ይህ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን የማይበጅ የሚሲዮናውያንን ዕቅድ ያሳካ ነበር። ይህም ጊዜ ‹ኢየሱሳዊያን› ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ሲመኙት የነበረውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለማፈራረስ ለእጭር ጊዜ ቢሆንም ፍላጐታቸውን ለማርካት የቻሉበት ጊዜ በመሆኑ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጠባሳውን እስከ መቼውም አትረሳውም።
- ጴጥሮስ ፖኤዝ የስፔን ተወላጅ ቢሆንም የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ነበር። ከቀለም ትምህርቱ ጋር ‹ሃይማኖተኛ› እና ‹ካህን›ም ጭምር ነው። የተለያዩ የእጅ ሞያ፣ ሠዓሊ፣ ብረት ቀጥቃጭ፣ መሐንዲስ፣ ግንበኛና አናጢም ነበር። ጎርጎራ ላይ ያለውን ባለአንድ ፎቅ የንጉሡን ቤተ መንግሥት የሠራው እርሱ ነው።

ንጉሡ ሱሲንዮስ ለዙፋን ከመድረሱ በፊት ብዙ ፈተና ደርሶበት የችግሩን ቀን ያሳለፈው ከእፀደ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ተዘንግቶት፣ አክሱም ጽዮን ሔዶ ጸሎት ሲያደርስ የገባውን ቃል መሐላውን ረስቶ፣ የካቶሊክን እምነት በቃል ብቻ ሳይሆን በግብርም ተቀብሎ እንዲስፋፋ መፍቀዱ የበላበትን ወጪት ሰባሪ መሆኑ ሊቃውንት አባቶችን አሳዘናቸው።

ሱስንዮስ በሀገር ውስጥ ከሕዝበ ክርስቲያኑ የተነሣበትን ተቃውሞ ከውጭ ደግሞ አካባቢውን በበላይነት ይቆጣጠር ከነበረው ቱርክ በየጊዜው ይሰነዘርበት የነበረውን ጥቃት ለመቋቋም የሰውና የመሣሪያ ድጋፍ እንዲያኝ ለፖርቹጋል ንጉሥ ለዶን ፊልጶስና ለሮማ ፖፖ ጳውሎስ 5 ኛ በካቶሊኩ አለቃ በፓኤዝ እጅ ደብዳቤ ላኩ። በደብዳቤውም የሰፈረው ቃል፦

‹‹ከዚህ ቀደም የፖርቹጊዝ መንግሥት የዐፄ ልብነ ድንግል ርዳታ ጥያቄ ተቀብሎ ርዳታ ላከላቸው፤ በኋላም ልጃቸው ገላውዴዎስ አባታቸው የገቡትን ቃል ኪዳን አልፈጸሙትም፤ አሁንም እርስዎ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የካቶሊክን ሃይማኖት ተቀብላ ቤተመንግሥቱም፣ የቤተክህነቱም ሃይማኖት ካቶሊክ መሆኑ በግልጽ ካላሳወቁ በደብዳቤ የጠየቁትን ጉዳይ ለመፈጸም ያዳግታል። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወደ ሮማ ቤተክርስቲያን ከተደረበች ግን ማናቸውንም ርዳታ እናደርጋለን።» የሚል ነበር። ንጉሡም የደብዳቤውን መልዕክት የሚፈጽሙት መሆኑን ለሮማ ፖፖ ለኡርባን 8 ኛ ላኩ። በየካቲት 11 ቀን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሮማ ስር እንድትተዳዳር የሚል ዓዋጅ ከሱስንዮስ ቤተመንግሥት ታወጀ። በሮማ ፖፖ ተብሎ የተሾመውና ረዳት ኤጲስ ቆጶስ እንዲሁም ከ 18 ት ካህናት ጋር በመሆን አዲስ የፕሮፖጋንዳ ለውጥ አወጁ። በተጨማሪም፦

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መባሉ ቀርቶ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንድትባል።
- የምዕመኑም ጥምቀት ያለፈው እንደማይሠራ ተቆጥሮ እንደገና በካቶሊክነት እንዲጠመቁ
- ካህናቱ የነበራቸው ሥልጣነ ክህነት እንደሌለ ታስቦ እንደገና ከሚሲዮኖቹ ክህነት እንዲቀበሉ መደረግ።
- አብያተ ክርስቲያናት በእነርሱ ፖፖ እንዲባረኩ
- በዓላትና አጽዋማት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቀን አቆጣጠርና ባህል መሠረት እንዲፈፀሙ
- የቅዱሳንና መነኮሳት አባቶች አፅም ከቤተ ክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውስጥ ተቆፍሮ ወጥቶ እንዲቃጠል በንጉሡ ድጋፍ እንዲታወጅ ተደገረ።

በዚህ ምክንያትም ዐፄ ሱስንዮስ በጴጥሮስ ፖኤዝ እጅ ከነቤተሰቦቻቸው በሮማ ካቶሊክ ተጠምቀው ካቶሊክነታቸውን በገሀድ አስታወቁ። በዚህ ወቅት ካህናቱ፣ ሊቃውንቱና ምዕመናን አዋጁን አንቀበልም በማለታቸው ሰማዕትነት ተቀበሉ። በዚህ ዓመት ጴጥሮስ ፖኤዝ ጐርጐራ ላይ ሞተ። በዚህ ጊዜ ግብፃዊ ጳጳስም አቡነ ስምዖንም በሰማዕትነት ዐረፉ። ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ፣ ፍቅርተ ክርስቶስ ከሴቶች በሰማዕትነት ካረፉት ውስጥ ይጠቀሳሉ። በዚህም ጊዜ በትግራይ፣ በበጌምድር፣ በጐጃምና በሸዋ ያሉ ሊቃውንት ደንቀዝ እየሔዱ «ሰማዕትነት አያምልጥህ» እያሉ መጥተው በሱስንዮስ አደባባይ ከስምንት ሺህ በላይ ሕዝብ ረገፈ። ይህ በአንድ ወቅት የሆነው ብቻ ነው።

ዐፄ ሱስንዮስ የካቶሊክን ዕምነት ለማስፋፋት ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት ታምመው አንደበታቸው ተዘጋ፤ በእፄ ሱስንዮንስ ዘመነ መንግሥት የነበሩበት ቅዱሳን አባ ሐራ ድንግል፣ አባ ኖብ፣ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ፣ ቅድስት ፍትርተ ክርቶስ እና ሌሎችም ናቸው።

አፄ ፋሲል (ከ 1626-1662)

አፄ ፋሲል ሦስት ስሞች አሉት፤ አንደኛው ‹ፋሲል›፣ ሁለተኛው ‹ሥልጣን ስገድ›፣ ሦስተኛው ‹ዓለምሰገድ› የተባሉ ስሞች ናቸው። ከሦስቱ ስሞች ግን አንዱ በጣም የገነነና ስመ መንግሥቱም ነው። ስሙም ፋሲለደስ ነው። አፄ ፋሲል በዚህ በሃይማኖት ጦርነት ምክንያት ሀገሩ ታወከ።

አፄ ፋሲልም የአባታቸው እንዲህ መሆን አሳስቧቸው «እግዚአብሔር ይህን መዓት በአባቴ ላይ ያመጣባቸው ሃይማኖታቸውን በመለወጣቸውና የክርስቲያኖችን ደም በከንቱ በማፍሰሳቸው ተቀይሞ ነው፤ በጸሎታችሁና በሐዘናችሁ አባቴን አድንኑልኝ » (አባቴን በጸሎቱ የሚፈውስልኝ የበቁ አባት ፈልጉልኝ) በማለት በየገዳማቱ መልዕክት እንዲልክ አደረጉ። በወቀቱም የማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኩሴ አባ ዓምደ ሥላሴና ከዋልድባ ገዳም ከአባ ምዕመነ ድንግል ከተባሉ አባት ጋር በመሆን ሱብኤ በመያዝ የንጉሡን የአፄ ሱስኖስን እንደበት እንዲከፈት አድርገዋል። በዚህ ጊዜ ለልጃቸው ለአፄ ፋሲል «የእስክንድርያ ሃይማኖት ትመለክ፣ የሮም ሃይማኖት ትርከስ፣ ፋሲል ይንገሥ ብለው ባዋጅ አናግር» አሏቸው። ዐዋጁ ተነገረ። ሕዝቡም ተደሰተ የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት የደስታ ደወል ድምጽ አሰሙ። በየበረሃው የተሰደዱ ሊቃውንት፣ ካህናት መጻሕፍቶቻቸውን፣ ታቦቶቻቸውን ይዘው ወደየ አብያተ ክርስቲያናቸው ተመለሱ። ዓፄ ሱስንዮስም በነገሡ በ 28 ዓመታቸው ዐረፉ።

በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የተከናወነ ተግባር ቢኖር የሃይማኖት ክርክር ሲሆን የአፄ ፋሲል መንግሥት ሲደላደል በአጨጌ በትረ ጊዩርጊስ መሪነት ከአልፎንሶ ሜንዴዝ ጋር ለመከራከር ሊቃውንቱ ፈቃድ ጠየቁ። ንጉሡም ጉባኤው እንዲደረግ ወስነው ከሊቅ እስከ ደቂቅ በጐንደር ጉባኤ ተደረገ። የተዋሕዶዎቹ አፈ ጉባኤ የነበሩት ራሳቸው ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ነበሩ። በዚህም የሃይማኖት ክርክር ተዋሕዶዎች ረቱ።

በዚህ ሰዓት አፄ ፋሲል አልፎንሶን ከሀገር ለማስወጣት ስለፈለጉ የፈጸማቸውን ክፉ ድርጊቶች ለፖርቹጋል መንግሥት ለካቶሊክ ጳጳስ ምክንያቱን ገልጸው አልፎንሶን ጠርተው ይህ ሁሉ ደም የፈሰሰው በእናንተና በእንተ ምክንያት ነውና ከነተከታዮችህ ሀገሬን ለቅቃችሁ ውጡልኝ አሉት። እነርሱም ከጐንደር ወጥተው በትግሬ ፍሬሞና በምትባል ቦታ (ሥፍራ) ተደበቁ።

በፍሬሞና መደበቃቸውን ዓፄ ፋሲል ሰምተው በአስቸኳይ በምዕዋ በኩል ከኢትዮጵያ እንዲያስወጡት ወታደሮችን ላኩ። እነርሱም ከፍሬሞና መጥተው ከኢትዮጵያ ለመውጣት መረብ ተሻግረው ከባሕረ ነጋሽ (ከዮሐንስ አከን) ዘንድ አምሞኛል ብሎ ሰነበተ። ከዚያም ከጐንደር አብረው ለመጡት ሁለት ኢትዮጵያውያን የቅብዐትንና የጸጋ እምነት አስተማሯቸው። በዚህ ጊዜ «በኢትዮጵያ ሁለት እሾህ ተክዬባታለሁ» አለ ይባላል።

እነዚህ ሁለት እሾኾዎች፡- የቅብዓት እምነት /ለኤዎስጣቴዎስ ዘሰንኳ ጊዮርጊስ - ለጐጃም/፤ እና የፀጋ እምነት /ለተክለሃይማኖት (ቆረንጮ) - ለሸዋ/ ይባላሉ።

በዚህም ዘመን የጸጋና የቅብዓት እምነት ከተዋሕዶዎች ጋር ተከራክረው ተረትተዋል።

አፄ ፋሲል የጐንደርን ቤተ መንግሥት በመገንባት፣ አብያተ ክርስቲያናት በመትከልና የሃይማኖት አንቀጽ በመደንገግ ይታወቃሉ። በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የነበሩት ጳጳሳትን አባ እስትንፋሰ ክርስቶስ፣ አባ ምዕመነ ድንግል፣ አባ ዓምደሥላሴ ናቸው።

- የመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን መሠራት
- ዓርባ ዐራቱ ታቦት ፡- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያሉት የታቦት (የቅዱሳን) ብዛት አርባ አራት (44) ብቻ አይደሉም፤ በኢትዮጵያ ቢያንስ 4 ዐ,000 አብያተ ክርስቲያናት አሉ። በእነዚህም ውስጥ 40 ሺህ ታቦታት መኖራቸውን ይጠቁማል።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዓመት ውስጥ በአማካይ በቀን የ 3 ቅዱሳን በዓል ይከበራል። በዚህም ስሌት መሠረት ቢያንስ 10,200 ቅዱሳን በዓመት ውስጥ ይከበራሉ ማለት ነው። ከዚህ አኳኋን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታቦታቱም ሆኑ ቅድሳን ከ 44 እንደሚበልጡ እንገነዘባለን።

ታዲያ **44** ቱ ታቦት የሚለው ሐሳብ ከምን መጣ**?**

መልሱ፦ ዓርባ ዐራት ታቦታት በጐንደር ዘመነ መንግሥት በአንድ አካባቢ የተተከሉ አብያተ ክርስቲያናት ብዛት (ቁጥር) ለመጥቀስ ነው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የተተከሉት በዐራት ዓይነት ሰዎች አማካኝነት ሲሆን እነርሱም፦ በነገሥታት፣ በመኳንንት፣ በባላባቶች እና በሀገሩ ሕዝብ ናቸው።

ምዕራፍ - ሰባት

ከዘመነ መሳፍንት እስከ አፄ ኃይለሥላሴ

ከ 1760-1860 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ እንደቅርጫ ሥጋ የተከፋፈለችበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያንም እየተደመጠች ሔደች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የአሁኑን ይዞታዋን ማወቅ የሚቻለው በየጊዜው የደረሰባትን ወረራ ስናውቅ ብቻ ነው።

‹‹ዘመነ መሳፍንት›› የተባለበት ምክንያት ነገሥታቱን ለምሥል ብቻ አንግሠውና አስቀምጠው ሀገሪቱን የሚመሩት ዓምባገነን መሣፍንትና መኳንንት ስለነበሩ ዘመናቸው ዘመነ መሳፍንት ተብሏል። እነዚህ መሣፍንት እርስ በርሳቸው ስለማይስማሙ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ከውጭ ሀገር ማሣሪያ ለማስመጣት (ለማስገባት) በሚሲዮኖች አማካይነት ወደየመንግሥታቱ ይላላኩ ነበር።

ይህ ዘመን በእኛው መንግሥታት ቤተ ክርስቲያናችን የተደፈረችበት ዘመን ነው። በተጨማሪም ይህን ምክንያት አድርገው ሚሲዮኖቹ ሃይማኖታቸውን ለማሠራጨት አመቺ ጊዜ የሆነላቸው ዘመንም ነው። በየመኳንንቱ ቤትም እየተቀመጡ አማካሪዎች ሆኑ።

ለምሳሌ፦ በሰሜኑ ክፍል ኤርትራን ብንወስድ ቆለኞቹ ወደ እስልምና ሃይማኖት የተለወጡት ዘመን ሲሆን <u>ቢኒአመር</u> የሚባሉት ክርስቲያኖች <u>በመሐመድ አትማን አልሚርጋን</u> ተሰብከው ወደ እስልምና ገብተዋል። እንዲሁም ማሪያና (ቤተ አሰገደ) የሚባሉት ደግሞ ክርስቲያኖች <u>በአድ ሻይክ</u> በሚባሉ የእስላም ሚሲዮኖች ተሰብከው ሃይማኖታቸውን ወደ እስልምና ቀይረዋል።

በዚህ ዘመን በካህናት እጦት ምክንያት ብዙዎች ክርስቲያኖች አምነት እንጂ ጥምቀት አልነበራቸውም። <u>ለምሳሌ</u>፦ ሞቻ በተባለው (በምዕራቡ) በኩል ግራኝ ያላፈረሳቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። እነዚህ ክርስቲያኖች በየሳምንቱ አሑድ ወደ ቤተክርስቲያኖች በሚሰበሰቡበት ጊዜ ቀድሶ የሚያቆርባቸው ቄስ ስላልነበራቸው ልጆቻቸውን አዝለው ቤተክርስቲያኑን እየዞሩ «ንስእለኪ ማርያም» እያሉ ልመናቸውንና ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር አሰምተው ይመለሱ ነበር።

በዚህ በጨለማ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምታደርገውን አጥታ ስትቸገር፣ በመከራዋ ላይ መከራ ለመጨመር በመሐል አገር ያለውን ክርስቲያን ደግሞ ለመከፋፈል የሮማ ፖፖዎች የላቲን ሰባኪዎችን በብዛት ይልኩባት ነበር።

በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን ብዙ ቅርሶቿን ተነጥቃ የተወሰደባት ዘመን ነው። እንግሊዞች፣ ፈረንሳዮች፣ ቱርኮች፣ ፖርቹጋሎችና ሌሎችም በወንጌል ስም ንዋያተ ቅዱሳትን እየዘረፉ ይወስዱባት የነበረበት ዘመን ነው። አልፎ ተርፎም የራሷ ሰዎች (አገልጋይ) ቅርሶቿን የሸጡበት ዘመንም ነው። በዚህ ዘመን በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም ከነበሩን አያሌ ቦታዎችን የተነጠቅንበት ዘመንም ጭምር ነው።

በዚህ ጊዜ በየምክንያቱ ባለቤት የሌለው ንብረት ሆኖ በአርመኖችና በግሪኮች ብዙ ንብረት፣ ርስት(ጉልት) ተወስዶባታል። ለምሳሌ ጥንት ጎልጎታ ውስጥ የታሪክ ቦታዎች ያሏቸው ግሪክ፣ አርመን፣ ሶርያ፣ ኢትዮጵያና ግብፅ ሲሆኑ ከኢትዮጵያ በስተቀር ይዞታቸው ይዘው ሲገኙ ኢትዮጵያ ግን የደር ሡልጣን ገዳሟን በግብፃውያን ተነኮለኛ መነኮሳት ይዞታዋን ተነጥቃለች።

በዘመነ መሳፍንት የነበሩ ነገሥታት፦

1. ዐፄ ኢያሱ 3 ኛ
2. ዐፄ ሕዝቅያስ
3. ዐፄ በእደ ማርያም 2 ኛ
4. ዐፄ ሰሎሞን
5. ዐፄ ዮናስ
6. ዐፄ ዲሜጥሮስ
7. ዐፄ ጓሉ(ዕገ C ለ ጽዮን)
8. ዐፄ ኢዮአስ
9. ዐፄ ጊጋር
10. ዐፄ በእደ ማርያም 3 ኛ
11. ዐፄ ኢያሱ 4 ኛ
12. ዐፄ ገብረ ክርስቶስ
13. ዐፄ ሣህሉ
14. ዐፄ ዮሐንስ 3 ኛ ናቸው።

አፄ ቴዎድሮስ 2 ኛ ዘመነ መንግሥት (1845-1860)

በኢትዮጵያ የነገሥታት ኃይል ደግሞ በስማቸው ብቻ ለመግዛት መሣፍንት በገነኑበት ዘመን ይልቁንም በኢትዮጵያ በምዕራብና ሰሜን የቱርክና የግብፅ መንግሥት ተስፋፍቶ ራሷንም ኢትዮጵያን በሚያሠጋት ጊዜ በኢትዮጵያ ምዕራብ ቋራ በተለይ ሻርጌ ከሚባለው ሥፍራ ምንም እንኳ የነጋሢነት ዘር ባይኖራቸውም ስማቸው ከመግነኑ ጋራ የአሽናፊነት ድል ያላቸውን አንድ ሰው አስነሥቶ ኢትዮጵያ የተፈራች ሆና እንድትኖር እግዚአብሔር ስለፈለገ ‹ኃይሉ› የሚባሉ የቋራ ተወላጅ ከደንቢያ ባላባት ከሚወለዱት ከእመት አትጠገብ ልጅ ካሣን (በኋላ ቴዎድሮስ የተባሉትን) አስነሣ። በ 1811 ዓ.ም የተወለዱ ናቸው። እናታቸው በድህነት ምክንያት በኮሶ ሽያጭ ይተዳደሩ እንደነበር ታሪካቸው ይናገራል።

ልጅ ካሣ በልጅነታቸው አባታቸው ስለሞቱ ከእናታቸው ጋር ተቀመጡ፤ ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ደጃች ክንፉ በትምህርት እንዲያድጉ ልጅ ካሣን ማኅበረ ሥላሴ ወደሚባለው ገዳም ወስደው ለመነኮሳቱ ሰጧቸው። በዚህ ገዳም ዳዊትን ጨርሰው ሌላውን ትምህርት በሚቀጥሉበት ጊዜ የንግሥና ፍላጎት የነበረው ደጃች ማሩ የሚባል በመሳፍንቱ ቂም ይዞ ስለነበረ ገዳሙ ውስጥ በሚማሩበት ልጆች ብድር ለመመለስ ሕፃናቱን ገደላቸው። ልጅ ካሣ ግን ከዚህ አምልጠው ወደ አባታቸው ሀገር ሸሽተው ተቀመጡ። በዚያ ጊዜ ቋራ ከነበሩት ሽፍቶች ጋር ተደባልቀው የዘመቻ ዕቅድና የጦር መላ ተማሩ። ሽፍትነትንም ትተው ወደ ነገሥታቱ ቤት በመግባት የወታደርነትን ሥራ እየሠሩ ኖሩ። ስናር (ሱዳን) በሚባለው ስፍራ ከግብፆች ጋር ጦርነት በተደረገ ጊዜ ብዙ ጀብዱ ስለፈጸሙ ዝናቸው በያለበት ተሰማ።

ስለዚህ እንደዚህ ያለውን ጀግና በጋብቻ ገመድ አስረው ከሥልጣናቸው በታች ለማድረግ ሲሉ በዚያ ጊዜ ለስሙ ዘውድ ጭኖ በጐንደር ይቀመጥ የነበረው የሦስተኛ ዮሐንስ ባለቤት (የራስ ዓሊ እናት) እቴጌ መነን የልጅ ልጃቸውን ወይዘሮ ተዋበችን በሚስትነት ለልጅ ካሣ ዳሩላቸው። ይሁን እንጂ ልጅ ካሣ ዋናው ሐሳባቸው መላዋን ኢትዮጵያን ጠቅልለው ከሥልጣናቸው በታች ለማግባት እንጂ በዚህ ጋብቻ ምክንያት ለእቴጌዎቱና ለልጃቸው ለራስ ዓሊ ተገዢ ሆነው ለመኖር አልፈቀዱምና ባለቤታቸውን ተዋበችን ይዘው ሸፈቱ። በዚህም ወቅት ጦርነት ገጥመው ድል ስላደረጉ ዝናቸው በሁሉ ዘንድ ተሰማ። ኢትዮጵያንም ከመሳፍንት እጅ ለማላቀቅና በአንድ ንጉሥ እንድትመራ እና በሃይማኖትም አንድ እንድትሆን ስለፈለጉ ብዙዎችን ነገሥታት አሸንፈው አያሌ ክፍላተ ሀገራትን ተቆጣጠሩ። በዚህ ምክንያት ሀገረቷን አንድ አድርገው ለመግዛት ድፍረት ስለሰጣቸው ኢየሩሳሌም ድረስ ለመዝመትና ኢየሩሳሌምንም ከቱርክ መንግሥት ለማስለቀቅ ያስቡና ይጥሩ ነበር።

አፄ ቴዎድሮስም በጦርነት አሸንፈው ሁሉንም ማረኳቸው። ከዚህ በኋላ ደጃች ካሣ በሠራዊታቸው ታጅበው በድል አድራጊነት ደጃች ውቤ አሠረተውት ወደነበረው ወደ ደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ሴቱም ወንዱም በዕልልታና በጭብጨባ ተቀበሏቸው። ወዲያው በ 3 ኛው ቀን በ 1847 ዓ.ም የካቲት 5 ቀን በዕለተ እሑድ በጳጳሱ እጅ (አቡነ ሰላማ) ተቀብተው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ።

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የተከናወኑ ተግባሮች

- በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ አባ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፤
- የደብረ ታቦር ጉባኤ፤
- የብዙ አብያተ ክርስቲያናት መታነጽ
- የአለቃ ገብረ ሐና መነሣት
- የእንግሊዞች መምጣትና የመቅደላ ዝርፊያ

የአለቃ ገብረ ሐና መነሣት

በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት በድሮው የደብረ ታቦር አውራጃ ፎገራ ወረዳ ናባን ጉዮርጊስ በ 1814 ዓ.ም ተወለዱ። የመጀመሪያ ትምህርታቸውን በአካባቢያቸው፣ ቅኔ በጎጃም፣ ጸዋትወ ዜማ ከመምህር ወልደ አብ ወልደማርያም ጎንደር፣ አቋቋም ከባሕታዊ ገብረ አምላክ፣ ድጓና ትርጓሜ መጻሕፍትን ከዐቃቤ ስብሐት ገብረ መድኅን ተምረዋል። በ 26 ዓመታቸው ጎንደር ሊቀ ካህንነት ተሹመው ለ 7 ዓመታት ማገልገላቸው ይነገራል። በዚህ ወቅትም በትርጓሜ መጻሕፍት ዕውቀታቸውና በስብከታቸው በጎንደር የታወቁ ነበሩ።

አለቃ ገብረሐና ቀልድ አዋቂነታቸው እየታወቀ የመጣው ለፍትሐ ነገሥት ሊቅነታቸው በዳኝነት እየተሰየሙ በቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት እየተሾሙ ባገለገሉበት ወቅት ነው። ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያን ወደር ከማይገኝላቸው ሊቃውንት አንዱ ናቸው። አለቃ ገብረ ሐና ከባሕታዊ ጸዓዳ ገብረሥላሴ ጋር በመሆን በጎንደር አቋቋም ስልት የመቋሚያውን የአካል አንቅስቃሴን ጨምረው ዝማሜውን አዘጋጁት። ባሕታዊ ጸዓዳ «ከእንግዲህ እኔ ወደ ዓለም አልመለስም አንተ ይህን ስልት አስተምር» ብለው አደራ አሏቸው። ይኸን የአቋቋም ዝማሜ ለልጃቸው ለተክሌ አስተምረውት በስሙ «የተክሌ አቋቋም» እየተባለ በመጠራት ዋና ማስመረቂያ ቦታው ልጃቸው የደብር አለቃ ሆነው አቋቋም ባስተማሩበት ደብረ ታቦር ኢየሱስ ሆኖ ቤተክርስቲያን እየተገለገለችበት ይገኛል።

አለቃ ገብረሐና እስከ አፄ ምኒልክ ቢኖሩም በዕድሜያቸው መጨረሻ አካባቢ ዝምታን በመምረጥ ቀድሞ በሠሩት (በቀልዳቸው) ይጸጸቱ ነበር። አንደበታቸውን ከነገረ ዘርቅ በመከልከልም ከጥሩ ምግብና ከጥሩ መጠጥ ተቆጠቡ። ቅዱሳን መጻሕፍትንም ሰብስበው «መሳቂያና መዘመበቻ አደረግኋችሁ» እያሉ ይቅርታ ይጠይቋቸው እንደነበር ይነገራል። በዚህ ሁኔታ ከሰነበቱ በኋላ በ 84 ዓመታቸው የካቲት 24 ቀን 1898 ዓ.ም ዐርፈዋል።

እንግሊዞችና የመቅደላ ዝርፊያ

እንግሊዞች ባሕር ተሻግረው፣ ድንበር ጥሰው፣ ክተት አስነግረው አፄ ቴዎድሮስን ጦርነት ገጥመው በውጊያው የእንግሊዝ ጦር በማየሉ አፄ ቴዎድሮስ ባሮቻቸውን አሰናብተው ራሳቸውን ገደሉ፤ ጦርነቱም በፈረንጆቹ አሸናፊነት ተፈጸመ። ከዚያ በኋላ በመቅደላ ጦርነት በእሳት ከመጋየታቸው በፊት ንጉሡ የሰበሰባቸው መጻሕፍት በሙሉ እንዲዘረፉ ተደረገ። ቁጥራቸው ከ 3000 በላይ የሆኑት እነዚህ ውድ ሀብቶቻችን ተዘርፈው ባህር ማዶ ተሻገሩ። የመቅደላ ዝርፊያ በብዛቱ ተወዳዳሪ አይገኝለትም። ቤተክርስቲያን በዚህ ወቅት ከ 3 ቢሊዮን ፖውንድ በላይ የሚያወጡ ንዋያተ ቅድሳትና ቅርሶች ተዘርፋለች።

እነዚህ የሀገራችን ውድ ስጦታዎች ወደ ተለያዩ የእንግሊዝ የትምህርት ተቋማት፡- ´ካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ´፣ ´ሮያል ላይብረሪ´ እና ወደ ተለያዩ ቤተ መጻሕፍት ተወስደው እየተጠቀሙበት ይገኛል። በመላው አውሮፓ ዝናቸው የተሠራጨው የእነዚህ ውድ ሀብቶች ሌሎችንም ዓይናቸውን በቤተክርስቲያን ሀብት ላይ እንዲተክሉ አደረጋቸው።

የዓፄ ዮሐንስ መነሣት **(1863-1881)**

አፄ ቴዎድሮስ ካረፉ በኋላ አፄ በዝብዝ ካሣ የተባሉት በአቡነ አትናቴዎስ እጅ በጥር 13 ቀን 1863 ዓ.ም በአክሱም ጽዮን ተቀብተው ነገሡ። ንጉሡም አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ተብለው ከነገሡ በኋላ ለኢትዮጵያና ለቤተ ክርስቲያን ያከናወኑት ተግባራት (ሥራዎች) አሏቸው። እነርሱም፡-

1. ጳጳስ ማስመጣት፡-

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የነበሩት ጳጳስ አቡነ አትናቴዎስ ይባላሉ። በተጨማሪም ከአስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ተላልከው አንድ ጳጳስ መጥቶ ከኢትዮጵያ ስፋት የተነሣ ስብከተ ወንጌልን ለማድረስ አይበቃም ብለው ዐራት ጳጳሳት አስመጥተው አንዱን ጳጳስ ለሸዋ /አቡነ ማቴዎስን/፣ አንደኛውን ለጐጃም /አቡነ ሉቃስን/ የቀሩትን ሁለት ጳጳሳትን አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ዮሐንስን በትግራይ ወንጌል እንዲሰበክ ጥረት አድርገዋል።

2. ኢትዮጵያውያንን በአንድ ሃይማኖት ለማድረግ የሠሩት ሥራ፡-

ተገድደው ወደ እስልምና የገቡትን እንዲጠመቁ በማድረግ ወደ ቀደመ ክርስትናቸው እንዲመለሱ አድርገዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ በሚሲዮናውያን ስብከት እንዳትከፋፈል ያደረጉት ጥረት ተጠቃሽ ነው። ሚሲዮናውያንን በሙሉ ከሀገሪቱ በማስወጣት ሁሉም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት እንዲጸና በማድረግ እንዲሁም የቅብዐትና የጸጋ ትምህርት ጨርሶ እንዲጠፋ አድርገዋል።

3. የቦሩ ሜዳ ጉባኤ፡-

ዓፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ ጦርነት ዐርፈው ዓፄ ዮሐንስ ከነገሡ በኋላ የካቶሊኮች መርዝ ውጤት የሆነው የቅብዐትና የጸጋ ከተታዮች ቤተ ክርስቲያን ላይ ከበፊቱ በበለጠ ተጠናክረው ተነሡ። በተለይ ከቅብዓቶች ጋር የነበረው የታላላቅ አድባራት ሙግት እየቀዘቀዘ ሲመጣ ጸጎች ግን አለን ማለት ጀመሩ። በዚህም ቤተ ክርስቲያንን አስቸግረዋት ስለነበር በ 1878 ዓ.ም በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ ላይ ጉባኤ ተደረገ። በጉባኤው ላይ የተገኙት ንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ፣ ንጉሥ ምኒልክ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ከቤተ መንግሥት ሲሆን፣ ከቤተ ክህነት አጨጌ ቴዎፍሎስ የነበሩ ሲሆን አፈ ጉባኤው አለቃ ኪዳነ ወልድ ከፍሌ፣ ረዳቶቻቸው አለቃ ተክለ ሥላሴ፣ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ሲሆኑ የጸጐቹ አፈ ጉባኤ ሥነ ጊዮርጊስ፣ አለቃ ሀብተ ወልድ፣ አለቃ ውቤና አለቃ ሌዊ ናቸው። ክርክሩም ተካሒዶ ተዋሕዶዎች ረቱ። ዓፄ ዮሐንስም ጸጎችን እንደቀጧቸው ይነገራል። በዚህም ምክንያት የጸጋ እምነት እየጠፋ መጣ።

(መሐዲስቶች) ድርቡሾች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሱት ጥፋት

- በ 19 ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ከሱዳን ተነስቶ የነበረው የፖላቲስና የሃይማኖት ንቅናቄ ነው። የእስልምና እምነት ማስፋፋትና ሱዳንን የሚገዙትን እንግሎ ግብፆች ማስወጣት ዋና ዓላማው ነው። እክራሪነትን የሚያራምድ እምነት። ይህ እምነት በ 7/8 ኛው መ/ክ/ዘ መታወቅ የጀመረ ቢሆንም ይበልጥ የተስፋፋ አብዛኛው የስፔን ክፍል በክርስቲያኖች በተያዘ ጊዜና ናፖሊዮን ግብፅ በወረረ ጊዜ ነው።
- አፄ ዮሐንስ በወቅቱ ያልታወቁ ክርስቲያን ሚሲዮናውያንን ለማጥመቅና ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ/ክ ለመመለስ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ከተዋህዶ ጋር አንተባበርም ብለው ሙስሊሞችና ሚስዮናውያን ወደ ሱዳን በመሸሽ ቀድሞ ከነበረው ሱዳን ጋር ተቀላቀሉ።
- ድርቡሽ በ **1880** ዓ.ም ከኢትዮጵያ ወጥተው ሱዳን በነበሩ እስላሞች እየተመሩ ወደ ጎንደር በመምጣት ጥር **10** ቀን የጎንደርን ከተማ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠሉ። ያገኙትንም ማርከው ወሰዱ።
- አፄ ዮሐንስም ንጉስ ተክለሃይማኖትን ቢልክም የንጉሥ ተክለሃይማኖት መሸነፍ ሲሰሙ **150** ሺህ ጦር አሰልፈው ወደ ከተማ በመዝመት ከድርቡሽ ሠራዊት የነበረው የድርቡሽ ጦርም ተጠናክሮ ተመለሰና ባደረገው ጦርነትም ዐፄ ዮሐንስም መጋቢት ሁለት ቀን **1881** ዓ.ም ዐረፉ።

- የድርቡሽ ጦርም በሰላያቸው በአማካኝነት ለሁለተኛ ጊዜ በለሊት ጎንደር ገብተው የተረፉትን ክርስቲያናት በማቃጠል ሕዝቡን አርደው ማርከው ተመለሰ። በዚህ አሉ የተባሉትን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መምህር ወልደ አብ ወልደሚካኤል፣ አባ ተክለሚካኤል፣ አባ ገብረ መስቀል፣ በግምጃ ቤት ማርያም ቤተ/ክ ተሰውተዋል።

አፄ ምኒልክ (1882-1906)

- ዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ሆነው ከ **1858 -1881** ዓ.ም ዓመት ከኖሩ በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነሐሴ **24** ቀን **1882** ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ ነገሡ። የዚያ ጊዜ ማኅተማቸው በሞጣ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት የሚል ነበር። ወደ አውሮፓ መልዕክት ሲልኩ በዚህ ባስቀረፀበት ማኅተም ነው።

አፄ ምኒልክ በዘመናቸው የሠሯቸው ሥራዎች

አፄ ምኒልክ የእንጦጦን ከተማ አድርገው መኖር ከጀመሩ ለኢትዮጵያና (ለቤተክርስቲያን) ከፍተኛ ውለታ ውለዋል።

- የእንጦጦ ማርምና የቅዱስ ራጉኤል (ኤልያስ) ቤተክርስቲያን የገነቱ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የደብረ ቁስቋም ማርያም የቅዱስ ዑራኤልና ሌሎችን በርከት ያለ አብያተ ክርስቲያን እንዲሠሩ አድርገዋል(ሠርተዋል)።
- የአድዋን ጦርነት ታላቁ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ይዘው በድንግል ማርያም ተማፅነው ወደ አድዋ በመዝመት ታላቁ በር ፋሽስት ኢጣሊያን ድል አድርገው ተመልሰዋል። ቤተክርስቲያንም በዚህ በአድዋ ጦርነት «ኢትዮጵያ ተበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች። የሚለውን የቅዱስ ዋዲት መዝ 68 ÷31 ያለው ኃይለ ቃል መነሻ በማድረግ የኢ.ኦ.ተ.ቤክ ክርስቲያን ካህናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገራን ከወራሪ እየተከላከሉ የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጽባቸውን ታቦትና ቅድሳት ሥዕላቶችን ይዘው እግዚአብሔር የማሸነፍ ኃይል ለኢትጵያውን ይሰጥ ዘንድ በአንድ በኩል በጸሎተ ምህላ፣ በሌላ መልኩ ወደ ጦርነቱ የሚገባውን እያናዘዙ፣ የሚደክመውን እያበረቱ ወደ ጦርነቱ እየላኩ እነሱም ይሳተፉ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል።
- የአፄ ምኒልክ ሥራቸው በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ በግራኝ መሐመድ በካቶሊካውያንና በዘመነ መሳፍንት በነበረው መከፋፈልና በአረማዊያን የፈራረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱና በአዲስ መልክ እንዲሠራም አድርገዋል። ለካህናቱ ለዲያቆናቱ ሰፊ መሬትም ሰጥተዋል።
- በኢየሩሳሌም የዴር ሡልጣን ገዳማትን ከግብጽ ጋር በነበረው ድርድር የኢትዮጵያ መነኮሳት መውጫ መግቢያ አጥተው ስለነበር ወደ ቱርክ መንግሥት መልእክተኛ ልከው የዴር ሡልጣን በር እንዲከፈት አድርገዋል።

- አፄ ምኒልክ ሀገራችን ኢትዮጵያ በትራንስፖርት፣ በመገናኛ ብዙኃን፣ በጀግንነት የታወቀችና የበለጸገች እንድትሆን አድርገዋታል። በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የነበሩ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ሲባሉ ሌሎች የታወቁና ለቤተክርስቲያን የሠሩ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ነበሩ ለምሳሌ አቡነ ሳዊሮስ አቡነ ቄርሎስ ይገኙበታል።

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ (1909-1921)

ንግሥተ ነገሥታት ሥልጣኑን የያዙት ከአባታቸው ቀጥለው ሲሆን ዕለቱ (የካቲት **4** ቀን) አባታቸው ባሠሩት በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ በዓል ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው ዘውድ ደፉ። ተፈሪ መኮንን በዚህ ወቅት አልጋ ወራሽነት ሥልጣን ተሰጣቷቸው።

በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር በመስከረም **4** ቀን **1919** ዓ.ም ተመሠረተ።

ኢትዮጵያ የራሷን ልጆች ጳጳስ ይሾምላት የሚለው በቅዱስ ሐርቤና በአፄ ዮሐንስ የተጠየቀው ጥያቄ ፍጻሜ አግኝቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ግንቦት **18** ቀን **1921** ዓ.ም አራት ኢትዮጵዊያን ጳጳሳት ካይሮ ላይ ተሾሙ እነርሱም፡-

ከጵጵስና በፊት የነበራቸው ስም		ከጵጵስና በኃላ የተሰጣቸው ስም
1	መምህር ደስታ	አቡነ አብርሃም
2	መምህር ወልደ ኪዳን	አቡነ ይስሐቅ
3	መምህር ኃይለማርያም	አቡነ ጴጥሮስ
4	መምህር ሐዲስ	አቡነ ሚካኤል

በአመቱም ሌላ አንድ ተጨማሪ ጳጳሽ ተሾመ። እሳቸውም አቡነ ቄርሎስ ይባላሉ። በ 1922 ዓ.ም የእስክንድርያ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ 19 ኛ ኢትዮጵያን በመጎብኘት ላይ እያሉ የደብረ ሊባኖስ እጨጌ የነበሩትን ገብረ መንፈስቅዱስ ጥር 1 ቀን በአዲስ አበባ በታአካ ነገሥት በዓታ ማርያምና ቤተ ክርስቲያን አቡነ ሳዊሮስ ትምህርት ቤት የሚስፋፍበትን ዓለማ እንዲከተሉ አድርገዋል። ለተማሪዎችም ዕቃ ጥራጥሬ ማብሰያ ብረት ምጣድ እንኳን ሳይቀር ይሰጡ እንደነበር ይነገራል።

ቤተክርስቲዬን በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን**(1922-1966)**

በአፄ ኃይለሥላሴ በ 1921 – 1966 ዓ.ም የነገሡ ሲሆን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዓመት ከግብፆ ፓትርያርክ ስትገዛ (ስትገለገል) ቆይታ ነፃነት ያገኘችው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። አገራችን ኢትዮጵያ በንግሥት ህንደኬ (በጃንደረባው ባኮስ) አማካኝት በ34 ዓ.ም ክርስትና የተቀበለች ሀገር ብትሆንም ከግብፅ ጳጳሳት ማስመጣት የጀመረችው ከ325 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ከዚሁ ዘመን ጀምሮ እስከ 1920 ድረስ 110 ጳጳሳትን አስመጥታለች። እነዚህ ጳጳሳት የምታስመጣቸው በነፃ ሳይሆን በብዙ ወርቅና ብር፣ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳት ሌሎችን ገጸበረከት እየሰጠች ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ ስትጠቃ ቆይታ በአፄ ኃይለሥላሴ ብርቱ ጥረትና ድካም ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም ከወገናችን ጽጵስና እና ፓትርያርክነት ለመሾም መብት አግኝታለች።

<u>በአፄኃይለሥላሴ ዘመን የተከናወኑ ተግባራተት</u>

- በ1940 ዓ.ም አምስት ኢትዮጵያን ቆሞሳት ተመርጠው መጥተዋል። አምስቱ ቆሞሳት (ጳጳሳት)

ከጽጵስና በፊት የነበራቸው ስም		ከጽጵስና በኃላ የተሰጣቸው ስም
1	እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ	ብፅዕ አቡነ ባስልዮስ
2	መምህር ገሪማ	ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
3	ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ	ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ
4	መምህር ዘርፈ ብርሃን	ብፁዕ ያዕቆብ
5	መምህር ጌታሁን	ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዮስ

- ከዚህ ዘመን አንስቶ ግብፃውያን በፍትሐ ነገሥት ውስጥ «ወስብእ ኢትዮጵያሰ ኢይሚሙ ሊቀ እማእማራኒሆሙ» ብለው ያለአግባብ ያሰፈሩትን ሥርዓት (ጽሑፍ) ተሠረዘ።
- ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ፣ ሊቀጳጳስ ተብለው ካይሮ ላይ በብፁዕ አቡነ ዮሳብ 2ኛ ተሹመው መጡ። በመቀጠል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሰኔ 21 ቀን በ1951 ዓ.ም በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ከሊቀጳጳስነት ወደ ፓትሪያርክነት መንበር ከፍ አለች። ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም የኢትዮጵ ኦ.ተ.ቤ/ክ የመጀመሪያው ፓትርያርክ ሆነ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ የሥልጣን እርከን ላይ ደረሰች።
- የፓትርያርክነት ሥልጣን ስታገኝ በራሷ ቋንቋ የሚያስተምሩ በራሷ ቋንቋ የሚቀድሱ ጳጳሳት በመሾም ወደየ አህጉረ ስብከት ልካለች። ኢትዮጵያ የራሷን የፓትርያርክ ወንበር ካገኘች በኃላ በየዘመኑ በተሸሙት ፓትርያርኮች በርካታ ጳጳሳት በመሾም በሀገሪቱ ሀገረ ስብከት በመደልደል የወንጌል አገልግሎቱን እንዲስፋፋ አድርጋለች በማስፋፋትም ላይ ትገኛለች።

የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ በፓትርያርክነት የመሩ አባቶች

1. ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ባሰልዮስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
2. ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
3. ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
4. ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
5. ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

እንደዚሁም በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተሠሩ ሥራዎች

- የግእዝ መጽሐፎች ወደ አማርኛ መተርጎም
- የኢትዮጵ ኦ.ቶ.ቤ/ክ መንፈሳዊ ኮሌጅ መከፈት
- ከ 33 ጊዜ በላይ ለእስረኞች የምሕረት አዋጅ ማድረጋቸው
- በዘመናቸው የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ከአቡነ ጴጥሮስና ከአቡነ ሚካኤል ጳጳሳት ጋር ከኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ጋር በመሆን ፋሺስት ኢጣሊያን ወግተው አብረዋል።

ቤተክርስቲያን በአምስቱ ዓመት በፋሽስት ኢጣሊያን የደረሰባት ጉዳት

በአፄ ኃይለሥላሴ በነገሡ በ 5 ኛው ዓመት በ 1928 ዓ.ም ኢትዮጵያ በግፈኛው ፋሺስት ኢጣሊያ ተወረረች። በጦርነቱ የሀገር ወረራ ብቻ ሳሆን ቤተክርስቲያን ላይም ትልቅ ጉዳት እያደረሰ ነው። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጦርነቱን መርቃ ታንኩን ባርካ በመክፈት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ መከራና ስደት እንዲደርስ በር ከፍታለች። ሲዊዲናውያን ፕሮቴስታንት ጋዜጠኛ አሌክስንደር ለፓፓው የጻፈው ደብዳቤ ጦርነቱን ባርከውና የጦር መሣሪያ እርዳታ መግዣ መስጠታቸውን ተቃውሟል። የካቶሊክ እምነት ተከታዮችም ለጦር መሣሪያ መግዣ የሚውል ገንዘብ ወደ ሙዳይ መጽዋት እንዲያስገቡ ይታዘዙ ነበር።

በዚህም ጦርነት ወቅትም 2000 ገዳማትና አድባራት ተቃጥለዋል፣ ፈራርሰዋል። 137,000 ልዩ ልዩ እንስሳት ማጥፋታቸውን ይነገራል። ብዙ ባሕታውያንና መነኮሳት፣ ካህናት ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው መስዋዕት ሆነዋል። ከእነዚህም ውስጥ የአቡነ ጴጥሮስና የአቡነ ሚካኤል የሌሎችም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ሰማዕትነት በአርያነት ይጠቀሳል።

ሰማዕቱ አብነ ጴጥሮስ

አቡነ ጴጥሮስ የመጀመሪያ ስማቸው መምህር ኃይለ ማርያም ይባል ነበር። ብፅዕ አቡነ ጴጥሮስ በ1875 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሥላሴ አውራጃ ፍቼ ከተማ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከፊደል እስከ ንባብ፣ እስከ ቅኔ፣ ከቅኔ እስከ የመጻሕፍት ትርጓሜን በጎጃም፣ በሸዋ በጎንደር ብሉያትና ሐዲሳትን በወሎ በሚገባ አጠናቀው ተማሩ። በመቀጠልም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሄድ ምንኩስናን ፈፀሙ። ከዚያም ከወንበር አገልግሎት ወደ ቤተ መቅደስ ተልዕኮ ደርበው አገልግሎት መስጠት ጀመሩ።

ብፅዕ አቡነ ጴጥሮስ ደብረ መንክራት ምሁር ኢየሱስ ገዳም፣ በዝዋይ ደ/ጽዮን ቅድስት ማርያም ገዳም በሊሎች ደብር አስተዳዳሪና መምህር ሆነው ተሹመዋል። የእፄ ኃይለሥላሴ የንስሀ አባት እንደሆኑ ይነገርላቸዋል። ከዚያም ግንቦት 18 ቀን 1921 አምስቱም ጳጳሳት አንድ ሆነው ጳጳስናን ተሹመዋል። ፋሺስት ከጣሊያን አገራችንን ሲወር እሳቸው ለኢጣሊያ ፋሽስት ሕዝቡ እንዳይገዛ እያሉ ያስተምሩ ስለነበር በፋሽስት አለቃ ግራዝያኒ ተይዘው ለኢጣሊያን ንጉሥ እንዲገዙ ቢነገራቸው እንዲህ ብለው መለሱለት። «ንጉሤ ሠማያዊ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ ንጉሥ ኃይለሥላሴ ብቻ ናቸው»።ከዚያም እንዲገደሉ ከተወሰነ በኋላ አቡነ ጴጥሮስም ለሕዝቡ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ እንዳይገዛ አውግዘው የኢትዮጵያም መሬትም እንዳትቀበለው ወግዝ ትሁን»ብለው ተናገሩ ከንግግራቻም በኃላ የጠላት ጦር በ11 ጥይት ተኩሶ ገደላቸው የቅዱስ ጴጥሮስ በረከት ይደርብን አሜን።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል

መዓረገ ጵጵስና ከመቀበላቸው በፊት አባ ኃይለ ሚካኤል ይባሉ ነበር። ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በቀደሞው ቤጌምድር ጠቅላይ ጋዛታ አፈረ ዋና ልጫ መስቀል ክርስቶስ በተባለ ቦታ ተወለዱ። በዚያም በተወለዱበትም አካባቢ ግንድ አጠገብ.... ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በጥምቀት እንደገና ሲወለዱ ስመ ጥምቀታቸውም ኃይለ ሚካኤል ተባሉ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የቤተክርስቲያን ትምህርት አደላድለው ከጨረሱ በኃላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ከነበሩት ከአቡነ ማቴዎስ መዓረገ ቅድስና ተቀበሉ። ከዚህም ሂደታቸው ትምህርታቸውንና ገብረ ገብነታቸው በሰዎች ዘንድ ስለተመሠረተ ይህም በቤተ መንግሥቱ ለመኳንንቱ፣ ለመሣፍንቱና ለወይዛዝርቱ አበ ነፍስ ለመሆን በቁ። በዚህም አገልግሎታቸው የዜና ማርቆስ፣ የዝቋላ ገዳም፣ የደብረ ጽጌ ዑራኤል ቤተክርስቲያን፣ በማኅደረ ማርያም በእልቅና ተሹው አገልግለዋል። በመቀጠልም በኮፕት (በግብፅ)ና በኢትዮጵ ቤተ ክርስቲያን መካከል ለረጅም ዘመናት ዘልቆ የነበረውን የጵጵስና ሹመት ክርክር ተፈቶ ኢትዮጵያውያን ወደ ጳጳስና ሹት መድረክ እንዲቀርቡ በተደረገ ጊዜ ለታላቁ ሹመት ከተመረጡት አባቶ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አንዱ ሆኑ። ከሌሎች አባታቶች ጋር ወደ ካይሮ በመሄድ ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም መዐረገ ጵጵስና ተቀበሉ።

ብፁዕ አባታችን በዚህ አገልግሎት ላይ ሳሉ ፋሺስት አገራችንን ስለወረረ ወራሪው በሳቸው ሀገረ ስብከት ስለደረሰ ለሕዝበ ክርስቲያን «ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውን ብቻ እንጂ የሌላ አይደለችም» በማለት ሲያስተምሩና ሲቀሰቅሱ እንደ ነበርና ከዚያም አልፎ በስብከት ጉዞ ላይ እንዳሉ እዚያው ሰምቢ ቀበሌ አጠገብ ከሚገኝ ጫካ ውስጥ በጠላት ጦር ተከበው በቆራጥነትና በአርበኝነት ሲዋጉ አንድ ለሊት ካደሩ ከሁለት አርበኞች ጋር ተማረኩ። እሳቸውም ሕዝቡም ለጣሊያን ፋስሽስት እንዲገዙ ቢመክራቸውም በእንቢተኛነት በመፅናታቸው ከሁለት ምርኮኞች ጋር የሞት ፍርድ ፈረዱባቸው። ጎዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም ከሁለቱ አራበኞች መካከል አድርገው በጥይት ደብድበው ገደሏቸው። ከተገደሉበት ቦታም ተነሥተው በጉራ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀምጧል። የሰማዕቱ አቡነ ሚካኤል ረድዔት አይለየን።አሜን።

ቤተክርስቲያን በዘመነ ደርግ (19 66-1983)

በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን የተጎዳችበት ሕዝበ ክርስቲያኑ፣ ካህናቱ፣ ዲያቆናት የተጎዱበት ዘመን ነበር። በዚህ ዘመን እግዚአብሔር የለም ተብሎ ስብከት የተሰጠበት ዘመን ጭምር ነው። በዘመነ ደርግ የቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የተገደሉበት ዘመን ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

ሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸው። የተወለዱት ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በማቻከል ወረዳ ደብረ ገነት ኤልያስ ሰበካ ነው የተወለዱት ቦታ የቤ/ክ ትምህርት ከተማሩ በኃላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከግብፃዊው ሊቀጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ዲቁና ተቀበሉ። ከዚያም ወደተለያዩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ቅኔ፣ የውዳሴ ማርያም፣ የቅዳሴ ማርያምና፣ የወንጌል ትርጓሜ፣ መጻሕፍተ ሐዲሳትን፣ የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ተምረዋል።

በ1930 ምንኩስና በደብረ ሊባኖስ ተቀበሉ ከዚያም በከተማ በአዲስ አበባ በተለያዩ ደብሮች በአስተዳዳሪነት ቤተ/ክርስቲያንን አገልግለዋል። ከዚም በ1940 ዓ.ም አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ የሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ሆነው

ተሹመው እያሉ በ1943 ዓ.ም የብፁዕ መቅደስ ፓትሪያርክ እንደራሴነት ደርበው ያዙ። አቡነ ባሰልዮስ ካረፉ በኃላ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ ሆነው ተሾሙ።

በፓትርያርክነት ዘመናቸው ለሰበካ ጉባኤ መሠረት በመጣል፣ በቤተክርስቲያኒቷ በልማት ራሷን ትችል ዘንድ የገቢ ማስገኛ ተቋማትን በመዘርጋት፣ የልማት ኮሚሽንን በማቋቋም፣ ሰንበት ት/ቤት መሥረት የቤተክርስቲያን ልጆች በውጭ ሀገር እንዲማሩ ማድረግ፣ ቤተክርስቲያን ዓለም ዐቀፋዊነት ይዘት እንዲኖራት በማድረግ ፈር ቀዳጅ ናቸው።

ደርግ ሥልጣን በያዘ በሁለተኛው ዓመት በ1968 ዓ.ም ወደ እስር ቤት ካስገባቸው በኃላ በግፍ ገድሏቸዋል። የተቀበሩበት ቦታ ተደብቆ ስለነበር በኃላ ግን በ1984 ዓ.ም ሐምሌ 4 ቀን ከራስ ካሳ ግቢ ተቆፍሮ ወጥቶ በግል ገንዘባቸው ባሠሩት በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አርፈዋል። ቤተክርስቲያንም በሲኖዶስ ሰማዕት ተብለዋል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር!!!